# ትክክለኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር



A calendar as ancient as Enoch, a Christianity dating from the birth of Christ, a computes as great as Demetrius, a land of refuge to the lord _ all this is here!

ኅሩይ ስሜ

# ትክክለኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ፤ አለሙ የተሳሳተውን የጎርጎርዮስ ዘመን አቆጣጠር መከተል፣ ዛሬ ከጌታችን ልደት በኋላ 2000 ዓ.ም መሆን

ኀሩይ ስሜ

2000 ዓ.ም

## ማውጫ

ለመፀሀፈ መንደርደሪያ የሆነው አጠቃሎ ....................................... 9
ምእራፍ አንድ
መግቢያ እና መነሸ ....................................................................... 11
ምእራፍ ሁለት
የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ታሪካዊ ፍንጮች ........................... 18
ምእራፍ ሶስት
የግብጽ /ቅብጥ/ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ
ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት ................................... 37
ምእራፍ አራት
ኢትዬጵያ እና ጌታችን ዘመነ ሥጋዌ ........................................ 58
ምእራፍ አምስት
የኢትዬጵያ ዘመን መቁጠሪያ ዮልዮሳዊ ነውን? .................. 63
ምእራፍ ስድስት
ክርስቲያናዊው ዘመን አቆጣጠርና
መንደርደሪያው የሥነ-መለኮት ትምህርት ................................ 73
ምእራፍ ሰባት
የምእራባውያን ዘመን አቆጣጠር አጭር ታሪካዊ አመጣጥ ... 86
ምእራፍ ስምንት
የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና የሄሮድስ
መንግስት ................................................................................... 96
ምእራፍ ዘጠኝ
የቅድስ ሉቃስ ወንጌል ታሪካዊ ማመልከቻና
አይሁዳዊው ጆሴፈስ የፃፈው የአይሁድ ታሪክ .......................... 121
ምእራፍ አስር
አቡነ አውሳቤዎስ ስለ ጌታችን ልደት የገለፀው ማስረጃ........ 126
ምእራፍ አስራ አንድ
ሊቁ ገማልያል ስለ የገሊላው ይሁዳና የጽፈት ዘመን
የተናገረው ማመላከቻ ................................................................. 132
ምእራፍ አስራ ሁለት
በዘመን መቁጠሪያው ላይ ያለ ተቃውሞ .................................... 139
መደምደሚያ ............................................................................ 144

## የጥናታዊው ፅሑፍ መንደርደሪያ ሆኖ የቀረበ አጠቃሎ

## (Abstract)

ለዚህ መጸሐፍ ጥናት ማዘጋጅያ አርእስት ትክክለኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር አለሙ የተሳሳተውን የጎርጎርዮስን ዘመን አቆጣጠር መከተልና ዛሬ ከጌታችን ልደት በኃላ 2000 ዓ.ም መሆን የሚል ሲሆን በዚህ ጥናት በጠቅላላ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ/ክ አባቶች በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ትክክለኛ ክርስቲያናዊ የዘመን መቁጠሪያን እንዳስረከቡን የሚያሳዩ የተለያዩ ፍንጮችን ከጥንታዊ የታሪክ ማስረጃዎች ጋር በማጣቀስና ጠቅለል ባለ መልኩ የጎርጎሪዮሳውያኑን ስህተት አጉልቶ የሚያሳይ ተደርጓል። ብሎም በህዝብ ዘንድ ስለ ዘመን መቁጠሪያው ያለውን ሃሳብ፣ ድጋፍና ተቃውሞን ጨምሮ የሚያሳይ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ያላት ልዩ የዘመን መቁጠሪያ ከጎርጎሪያዊው ጋር ሲነፃፀር በይበልጥ የተሻለ ክርስቲያናዊ ዘመን መቁጠሪያ የሆነ ሲሆን በዚህም የጌታን ልደት ዘመን በአግባቡ ያገናዘበና የዘገበ መሆኑን የሚያሳዩ ታሪካዊ ምንጮች ይጠቀሳሉ። በዋናነት ትኩረት የሚሰጠው ክፍል በሀዲስ ኪዳን ወይም በክርስትና ዘመን ባለው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ነው። በተቃራኒው ደግሞ የዩልዮስና ጎርጎርዮስ ዘመን መቁጠሪያ ብሎያትንና ሐዲስን በከፈለው በጌታ ልደት ቀንና ዓ.ም ላይ የተዛባና አንድ ወጥ ያልሆነ መሆኑን ለማሳየት የሚያስችል



ስራ የያዘ ክፍል ይኖረዋል። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ብዙ ኢትዮጵያውያን ደፍረው ይህንን ለመግለፅ ሲበረቱ አይታዩም። በምእራቡ አለም ደግሞ ሀቁን የማወቅ ችሎታና መረጃም ቢኖራቸው እንኳን የምእራባውያንን ስልጣኔ ብሎም የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን የበላይነት የሚያስደፍር ስለሚመስላቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ለመሸፋፈንና ለማደናገር ሲጥሩ እናስተውላለን። በዚህም ከራሳቸው ተርፈው ሌላውን አለም የተሳሳተ የዘመን መቁጠሪያ ተጠቃሚ እንዲሆን አድርገውታል። ስለምን ይህ እንደሆነ ጥናቱ የሚዳስሰው ክፍል ሲኖረው በተያያዥ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር አስመልክቶ ህዝቡ የሚያነሳው አስተያየት፣ ጥያቄ፣ ድጋፍና ተቃውሞ ሊዳሰስ የሚያሻው ክፍል ነው። በጠቅላላው በጥናቱ ዙሪያ ትክክለኛው የዘመን መቁጠሪያ የትኛው እንደሆነ ለማሳየት የሚያስችል ክፍል ሲኖረው በይበልጥም የጥናቱ ውጤት «የኢትዮጵያ አስራ ምእት የአለም አስራ ምእት ነው» ወደ የሚያስብልበት መንገድ የሚያሸጋግረን ነው የሚል ግኝት አለው።

# ምእራፍ አንድ

## መግቢያ

የሰው ልጅ ባሳለፈው ረዥም ታሪክ ውስጥ አያሌ ክስተቶች የየራሳቸውን ጥላና አሻራ ጥለው አልፈዋል:: በዚህ ረዥም ዘመን ውስጥ ሰው የታዘበውንና የገጠመውን አካባቢያዊና ማህበራዊ ችግሮች እንዲሁም ደስታዎች በትዝታ ማህደር ውስጥ ከትቦ ለትውልድ ያወርስ ዘንድ በማንኛውም አጋጣሚ ሲጥር ኖሮአል ይህንን ተከትሎ ይመስላል እንግዲህ የዘመን መቁጠሪያ /Calender/ እና የዘመን አቆጣጠር ለመጀመሪያ ጊዜ ለመመስረት የቻለው:: (Breasted, 1916)

በሌላኛውና በመንፈሳዊው ገፅታ ደግሞ የዘመን አቆጣጠር መፅሀፍ ዘመንን ባስገኘው በእግዚአብሔር የአለምን መፍጠር ወይም ፍጥረተ አለምን ተከትሎ ከመጀመሪያው ጥንተ እለት የተነሳ መሆኑን ያስረዳል በዚህ መልኩ የዘመን አቆጣጠርን የሚገልፀውና የሚያስተምረው የቤተክርስቲያን መፅሀፍና ትምህርት ባሕረ ሐሳብ (የሐሳብ ባህር ወይም የቁጥር እንዲሁም እውርን የሚመራ ወዘተ) በመባል ይገለፃል:: (አስራት እና ገብረሕይወት፣ 1987)

ከዘመን አቆጣጠር አጀማማር ጋር የተያያዘው ገለፃ እንደሚጠቁመው ህዝቦች የታሪክና የተፈጥሮ ክስተቶች ጋር ትስስር ያለውን ማህበራዊ ህይወት ለመመዝገብ ብሎም ለመጠበቅና አስቀድሞ ለመወሰን ይቻላቸው ዘንድ የተመሰረተ

ስለ መሆኑ ብዙዎች ይናገራሉ:: የዘመን አቆጣጠር የየትኛው ስልጣኔ ውስጥ ጉልህ ቦታ ያለውና ለዚህም በአለም ውስጥ የተነሱት የግብፅ፣ የባቢሎን፣ የቻይና፣ የቀይ ህንድ የኢንካና አዝቴክ እንዲሁም የማያ ስልጣኔዎች ለዚህ ህያው ምስክሮች ናቸው (World History, 1950)

የዘመን አቆጣጠር ዋነኛ ጥቅሙ ለእርሻ ስራ የወራቶች፣ የወቅቶች ዑደትን አስቀድሞ ለመተንበይና ለማወቅ እንዲሁም አስፈላጊውን ዝግጅት ለመከወን፣ ለንግድና ለጦርነት ተዛማጅ ጥንቃቄዎችና ጉዞና ዘመቻ ለማድረግ፣ ለአስተዳደርና ለሃይማኖት መደበኛ ቀኖችንና በአሎችን ለመወሰን እንዲሁም ዘመናዊ አሰራርንና ቁጥጥርን ለመጀመር /Management/ የግድ የሚያስፈልግ ጥበብ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም::

በአለም ስልጣኔ ውስጥ ቀደምት የሆነውና ዘመናዊው የዘመን አቆጣጠር በግብፃውያን ከጌታችን ልደት በፊት በ3000 ዓመት ግድም የተጀመረ ሲሆን በ365 የፀሀይ ቀንና በ12 ወር ከ5 ቀን የተዘጋጀ ነበር (Gordon, 1970)

እንደ ባህረ ሀሳብ ዋነኛ አዘጋጅ ሊቅ አቡሻከር ደግሞ የባህረ ሃሳብ ቀመር እና ትምህርት ስለ ዘመን አቆጣጠር መጀመሪያ የሚነሳው በመጀመሪያ ከሙሴ ከዚያም ከሐዋርያት በማስከተልም ከየግብፅ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዲሜጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት የተሰጠ ጥበብ መሆኑን ነው:: ለማንኛውም ወደ ኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ስንመጣ በየትኛው የጥንት



ዘመንና በማን ዘመን ይቆጠር እንደነበር ሙሉ ማስረጃው በግልፅ አይታወቅም:: ነገር ግን ክርስቲያናዊው የዘመን አቆጣጠርን ከቅዱስ ድሜጥሮስ የባህረ ሃሳብን ትምህርት ቀጥሎም የደቀ መዝሙሩ የአቡሻከር ቅንብር ስለ መከተላችን ብዙና ግልፅ ማስረጃዎች አሉ:: (ጌታቸው፣ 1993)

ከዚህ ጋር የክርስቶስ ልደትን በተመለከተ ለመላው አለም የክርስቲያን ዘመን ወይም አመተ ምህረት መስጠት ተያይዞ በግልፅ እንደሚታወቀው በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞና ሀገራችን ካላት ቀደምት የብሉይና ኦሪት ግንኙነት ጋር ትክክለኛውን የጌታን ልደት ለመመዝገብ እንደረዳ ይታመናል::

በመሆኑም የኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር ከክርስቲያናዊው ዘመን / Christian era/ እንዴት እንደሚጀምር ብሎም በተያያዥ በህዝቡ ዘንድ ያለውን ግንዛቤና እውቀት ምን ያህል እንደሆነ ማጤን እና የፅሁፍ ማስረጃ መተው ለወደፊት ለሚመጣውም ትውልድ አስፈላጊና ወሳኝ ነው::

ከዚህም ባሻገር በዘመን አቆጣጠሩ ዙሪያ ባለው ተቀባይነትና ተቃውሞም የተጠቃሚውን ሀሳብ ከወዲሁ መረዳትና ጥያቄውንና አመለካከቱን መገምገም ከባህል መጠበቅና ቅርስን ከመንከባከብ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚያስችለው ያደርገዋል:: ስለሆነም ዘመን አቆጣጠራችን ካለው ማራኪና ልዩ ብሎም ጥልቅ ቅርስነት አኳያ በዙሪያው

በሚያውጠነጥኑ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ላይ ሰፊ ምርምር ማካሄድ እንዳለብን ጊዜው ጠቋሚ ያደርገዋል::

የጥናታዊው ፅሁፍ መነሻ /Problem/

የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ቀመር ከቅድመ አቡሻከር ጊዜ ጀምሮ የነበረና ፍፁም የጠነከረ ልዩ እሴት ሲሆን አቡሻከር ደግሞ በተደላደለው መሰረት ላይ የፀናና መልካም የሆነ አስተዋጽኦ አበርክቷል:: ነገር ግን ብዙ ከሚጠበቅብን ከኛ ኢትዮጵያውያን ስራ ስላልተሰራ መላው አለም ስለ ትክክለኛው የዘመን መቁጠሪያና ዓ.ም ሊያውቅ አልቻለም:: ከዚህም በዘለለ የዘመን መቁጠሪያውን ትክክለኛነት የሚጠራጠሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን መበራከታቸው አሌ የማይባል ሀቅ ነው:: ይህንን በመያዝ ምዕራባውያኑ የለተያዩ ነቀፌታቸውንም ሰንዝረዋል:: ስለዚህም ዋነኛው ዘመን መቁጠሪያው የተሳሳተና አገሪቷን ወደ ሰባት አመት የሚጎትት ነው እያሉ መናገራቸውን አዳምጠናል:: ይህ ችግር ለጥናቱ መነሻ በመሆን የነዚህን የተከናወኑትን የሃሳብና የእውቀት ልዩነት ለመሙላት ታሳቢ ያደረገ ፍንጭ ይኖረዋል::

ማረጋገጫና ጥቅም /Justification/

ትክክለኛውን የክርስቲያኖች ዘመን መቁጠሪያ መነሻን የያዘው /Christian era/ የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ ምንጩ የተከተተው በ«ባህረ ሀሳብ» የባእላት፣ የሰንበትና የቀናት



መቀመሪያ ወጥ ስራ ውስጥ ነው:: ይህ የባህረ ሀሳብ ቀመር እና ፍፁም ሚስጥር በአለም ላይ ትክክለኛውን የክርስቲያን ዘመን መጀመሪያ /Christian era/ በሰፊ ታሪካዊ ማገናዘቢያዎቹ ማመሳከሪያዎቹ እንዲረጋገጥ ያደረገ ሲሆን እነዚህን መረጃዎች በጥንቃቄ ለተረዳና ላነበብ ሰው የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ የአለም ወይም ትክክለኛው ዘመን መቁጠሪያ መሆኑን ለመረዳት አይቸገርም:: ነገር ግን ምዕመናንም እንኳን በዚህ ትምህርት እውቀት መጎብኘታቸው ያጠራጥራል::

ይህ ጥናት መጠናቱ የማህበረሰቡን ጠቅላላ ንቃተ ህሊና የሚገመግምና ባህሉንና ሃይማኖቱን በምን መልኩ መጠበቅና ማወቅ እንዳለበት ያስተምራል :: አያይዞም በአለም ላይ ያለውን የባህል ወረራና ሉላዊነት ንቅናቄ በአስተማማኝ ክንድ ለመመከት በቂ ዝግጅትን የሚፈጥር መድረክ በመሆን ያገለግላል :: ይህ ደግሞ በጠንካራ ሁናቴ ነገ ሊነሱና በባህልና በሀይማኖት እንዲሁም ቅርስ ላይ የተሰሩ የማጥላላትና የመናቅ ሃሳቦችና ጥያቄዎችን ከስር ምንጫቸው ለመረዳት ብሎም መፍትሄ ለማፈላለግ የሚያገለግልበት አመቺ ጉልበትን ይፈጥራል :: ከሁሉም በላይ ግን ስለ ሃይማኖታችን፣ ቤተክርስቲያናችንና ስለ ባህላችን ፍፁም የሆነ እና የታመነ መረጃ ማበርከት ስለሚያስችል ጥቅሙ የጎላ ነው ::

ጠቅላላ ዓላማ /General Objective /

በጠቅላላ ላለው እውቀት ዝንባሌ አስተሳሰብና አስተያየት በዘመን መቁጠሪያው ላይ ሰፊ ጥናት ማበርከት

የጥናቱ ንዑሳን አላማ /Specific Objectives/

ለዘመን መቁጠሪያው ያለውን ድጋፍና ተቃውሞ ምክንያት ማወቅ

1. በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ክፍሎች በማጥናት ስለ ዘመን መቁጠሪያው ያላቸውን ዝንባሌና አስተያየት መረዳት
2. ስለ ዘመን መቁጠሪያው ያለውን ጠቅላላ እውቀት፣ ትክክለኛነትንና ብቃት በህብረተሰቡ ዘንድ ማስተዋወቅ
3. በዘመን መቁጠሪያው ላይ ያለውን ጠቅላላ ግንዛቤ ከተለያዩ አቅጣጫዎችና መደቦች መተቸት

የጥናታዊው ፅሑፍ ጥያቄዎች /Research Questions /

የጥናቱ ጥያቄ የሚሆነው የሕዝቡ ጠቅላላ እውቀት በዘመን መቁጠሪያውን ትክክለኛነት በመገንዘብ ደረጃ ምንድን ነው የሚል ነው? በማስቀጠልም

1. ዘመን መቁጠሪያው አለም አቀፋዊ ትክክለኛ ይዘትና ቀመር ከክርስቶስ ልደት መጀመሪያ ዓመት /Christian era/ ሲለካ በኛ ትክክል መሆኑን ማሳየት
2. ማህብረሰቡ የዘመን መቁጠሪያውን ቀጣይነት በምን ያህል እየተንከባከበና እያረጋገጠ ነው?



3. ዘመን መቁጠሪያው ይቀየር የሚል ተቃውሞ ካለ የተቃውሞ ምክንያት ምንድን ነው?
4. የጎርጎርዮስን ዘመን መቁጠሪያ መውረስ ይገባል ለሚሉ ክፍሎች ዋነኛ ምክንያታቸውና ምንጬ ምንድነው የሚሉትን ያካተተ ይሆናል?

<u>የጥናቱ ስልት /Methodology/</u>

በዚህ ጥናት ውስጥ በብቸኝነት እና በዋናነት የጥናት ስልት በመሆን የሚሰራበት ዘዴ ሰነዶችን የመመርመር /analysis on texts and documents/ ብቻ ሲሆን በጣም ውስን በሆነ መልኩ ሰዎችን ስለ ዘመን መቁጠሪያው ያላቸውን አስተያየት አስመልክቶ ቃለ መጠጥቅ ይደረጋል::

<u>ዋቢ መረጃዎች /Source/</u>

ከድህረ ገጽና በተለያዩ ጊዜዎች በዘመን መቁጠሪያው ዙሪያ የተደረጉ ክርክሮች የታሪክ መፅሀፎችና የቤተ ክርስቲያናችን አዋልድ መፃህፍት በማገናዘብና በማመልከት በዋቢነት በማጣቀስ ግልጽ የሆነ መረጃ ለማቅረብ ይሞከራል:: ከዚህ ውጭ የጕርጕሪያዊውን ሀሳብ ለማረጋገጥ የተፀፉ ስራዎችን ከመረጃ መረብ በማሰባሰብ አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም እንዲሰጥ ለማድረግ ታስቧል:: ይህም ጕርጕሪያውያኑ ስለ ልዩነታችንና ስለ ክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ያሰፈሩትን ስራ ስህተቱን አጉልቶ ያሳየዋል የሚል ሀሳብ

አለን። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ስለ አቆጣጠሩ የተፃፉ የተለያዩ መፀሀፍትንም ለመዳሰስ ጥረት ይደረጋል።



## ምእራፍ ሁለት

### የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ታሪካዊ ፍንጮች

ዘመንን የሰው ልጅ መቁጠር የጀመረበትን ጊዜ በታሪክ መርምሮ ለመድረስና መረጃ የሚሆኑ ተጨባጭ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ለማቅረብ እጅግ ያስቸግራል። ይህ የሆነበት ምክንያት ዘመኑ እጅግ ሩቅ ከመሆኑ የተነሳ ነው። ነገር ግን በጥቂቱ ያህል የሰው ልጅ ዘመንን ለመቁጠር ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል ዋነኛው በአመት ውስጥ የተከሰተን ታላቅ ክስተትና የሳደረውን ተጽእኖ ከዘመን አቆጣጠሩ ውስጥ በመጨመር አንድ ወጥ አቆጣጠርን ለመመስረት ሥእላዊ መግለጫ የመፍጠሩ ሁናቴ አንዱ ዘዴው ሆኖ ተገኝቶአል። ይህን መሰል ጥንታዊና ቅድመ ታሪካዊ የዘገባና የዘመን አቆጣጠር በጥንት ጊዜ በአሜሪካ ይኖሩ የነበሩ የዳኮታ (Dakota) ቀይ ህንዶች ይጠቀሙበት የነበረ ዘዴና ጥንታዊውን ሰው የሚወክል ሂደት መሆኑን ማህበረሰባዊ ታሪክ ያረጋግጣል።[1]

ይህን ካልን ዘንድ አለማችን ካስተናገደቻው ብዙ ታሪካዊ ክንውኖች መሃል የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልና የክርስትና ሐይማኖት ያሳረፈውን የሚያህል በጐ ተጽእኖን የሚወዳደር ምንም ነገር አልተገኘም። ይህ አለማቀፋዊ እውነታነቱ ከሥነ-መለኮት ትምህርት ብቻ

የሚመነጭ ሳይሆን በታሪክም ተአማኒነት ያለው ስለ መሆኑ ብዙ አያነጋግርም:: ስለሆነም የጌታችን ልደት ውሎ አያደር አለም አቀፍ የዘመን መቁጠሪያ ድንበርና የአዲስ ዘመን ከፋች (beginning of the Christian era) መሆኑን ምእራባውያን፣መለካውያን ምስራቃውያኑ (Greek Orthodox) እንዲሁም በኛ ዘንድ ያለው ዘመን መቀጠሪያ ህያው ምስክር ነው:: ስለሆነም የጌታችንን የልደት ዘመንን በቅጡ መረዳት ዘመነ ሐዲስን ወይም ዘመነ ክርስትናን (Christian era) በጥልቅ ለማወቅ እንዲሁም የዘመን መቁጠሪያን ለመመስረት በጣሙን ውስኝና ያለ እርሱ የማይቻል መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል::

ይህ እወነታ ደግሞ የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያና የምእራቡ ዓለም የሰባት ወይም ሰምንት አመታት ልዩነት እያሳየ እንዲገኝ ዋናው ምክንያት ሆኖአል ወደ ሌሎቹ ተዘዋውረን ታሪካዊ ዳሰሳን ከመስጠት በፊት ስለ የራሳችን የዘመን አቆጣጠር አመጣጥ ምንነትና ትውፊት ወሳኝ የሆኑ ታሪካዊ ምልከታዎችን ማየት እንዳለብን ግልጽ ነው:: የክርስትና ሐይማኖት ከአምላካችን ከክርስቶስ ጀምሮ እዛሬ ላይ ኦርቶዶክስ ርትእት እስክትባል ድረስ ቅዱሳን ሐዋርያት ብሎም ሐዋርያነ አበው ከዚያም ጳጳሳት አባቶች እያለ ተያይዞ መምጣቱን በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ እና አዋልዳት ንባብ ላይ ተጠቅሶአል:: ይልቁንም በፊት አስቀድሞ በጌታ ልደት ዘመን



በግብፅ፣ ሰሜናዊ ሱዳን፣ እና ኢትዮጵያ አምላክ በሰደት መኖሩ በኋላም በዘመነ ሐዋርያት በግብፅና፣ በሰሜን አፍሪካ ፣ በሶርያ እና በአረብ ሀገር ድረስ ወንጌል መነገሩ ስለ አምላክ መወለድ መበሰሩ ብሎም ይህ ሁሉ መቼ እንደሆነ ከዘመኑ ጋር መሰበኩ ተዘግቦአል::[2]

ኢትዮጵያውያንም የእዚህ እፃ ተቋዳሾች እንደሆኑ በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ በግልጽ እንደተፃፈው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በ34/35 ዓ.ም የክርስትናን ጥምቀት በረድኡ በቅዱስ ፊሊጶስ ተጠምቆ ወደ ሀገሩ ደስ እያለው እንደገባ ይገልፀልናል (የሐሥራ8:26) [3]

በዚህም ስለ ጌታ ልደት የዘመነ ፍዳ ህልፈት የአመተ ምህረት መሰጠትን በጥልቅ ከሚያወሳው ከረድኡ ፍሊጶስ ተረድቶ ለትውልድ እስከ ትውልድ እንዲተላለፍ አድርጓል:: ይህ ሲባል የጌታ ልደት ዘመን በትክክል ተዘግቦ እኛ ጋር ስለ መድረሱ በሌላም ወገን ማረጋገጥ ይቻላል:: ይኸውም የግብጽ የመጀመሪያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው እና የክርስትናዋ መንበር መስራቾ ቅዱስ ማርቆስ ከወንጌሉ ጋር የጌታን የልደት ዘመኑን ከልደቱ ታሪክ ጋር አስተምሮ ለቅዱሳኑ ሐዋርያነ አበው ያወረሰው እስከ ቅዱስ ድሜጥሮስ (230 ዓ.ም) ሊቀ ጳጳስ እና የባሕረ ሐሳብ መስራች ቀጥሎ ሲወርድ በ13ኛው ክ/ዘመን ላይ በአባ አቡሻከር ማብራሪያ የሚሻገረው የኛው የባሕረ ሐሳብ ትምህርትና ዘመን መቁጠሪያ የጌታችንን የልደት ዓመት እና

ቀን በትክክለኛው እና በእውነታኛው ቀንና ዓመት ላይ ዘግበው እንዳወረሱን አመላካች ነው፡፡

ይህንን ተከትሎ በትውፊት እንደሚነገረው «ከጌታችን እግር ስር በልደቱ ጊዜ ከስገዱት የጥበብ ሰዎች አንዱ ኢትዮጵያዊ ነው» የሚባለውንም ማጤን የስፈልጋልስ[4] በአንድምታ ወንጌል ዘ ማቴዎስ ምእራፍ 2 ቁጥር 1 ጀምሮ ስለ ሰብአ ሠገል (የጥበብ ሰዎች) በሚገልጸው ክፍሉ ይህንን ማንበብ ይቻላል፡፡

« [የፋርስ ሰዎች ለሰብአ ሰገል] ደርሳችሁ መጣችሁን አሏቸው? አዎን አሉ፡፡ ምልክት አላችሁ አሏቸው፡፡ እናቱ ስንቅ ስጥታን ይህ ሁሉ ሠራዊት እየተመገበው ባያልቅ ክቡር ነገር ነው ከተማ ይዞ መግባት አይገባም ብለን በአፋአ ትተነው መጥተናል፡፡ አሉዋቸው እስኪ አሳዩን አሏቸው፡፡ ቢሄዱ ሲጤስ አገኙት ከዚህ የተነሳ በእሳት እንጂ አምልኩ ሲለን ነው ብለው በእሳቱ የሚያመልኩ ሆነዋል፡፡ » ይላል

ይህ የጥበብ ሰዋች ከፋርስ ተነስተው ጌታን ካዩ በኋላ ሀገራቸው ሲገቡ የገጠማቸውን እና የጤሰውም እመቤታችን የሰጠቻቸው የገብስ ዳቦ መሆኑን የሚያወሳ ለብዙ ታሪካዊና ሥነ- መለኮታዊ ሚስጢራት ማመላከቻ የሆነ ገፀ ንባብ ነው፡፡

እነኚሁን የጥበብ ሰዎች የፋርስ ነገሥታት የምሥራቅ ነገሥታት እንዲሁም ሰብአ ሰገል በማለት መጽሀፍ ተአምረ ኢየሱስ በምእራፍ ሰምንት ከቁጥርም 2-3 ጀምሮ



ይጠራቸዋል፡፡ በታሪክ እንደ ሚታወቀው በፋርስ ከገነኑት አምልኮዎች መካከል አንዱ የእሳት አምልኮ (fire worshiping persians and the Magai) እንደ ነበር ተዘግቦአል፡፡ ይህ በቁሙ የአንድምታውን ታሪካዊ አመጣጥ በማስረጃነት ያጠናክረዋል፡፡

ፀሀፊው በ1997 ዓ.ም ላይ እንደሚያስታውሰው በዝዋይ ሀይቅ ላይ በምትገኘው በደብረ ፅዮን ደሴት ላይ ባለችው በቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን አለቃ የነበሩት አባት ስለ ቦታው ታሪክ ሲናገሩ «የጥንቱ ኢትዩጵያውያን በእሳት ምልክትነት ያመልኩ ነበር ያሉትን በዚህ አጋጣሚ ለማስታወስ ይፈልጋል፡፡ ስለ ነገሩ በዝርዝር ሲያስረዱ እንዲህ እያሉ ይጀምራሉ፡፡

«በጥንት ጊዜ ዮዲት የምትባል ንግስት ተነስታ አብያተ ክርስቲያናትን እየተኮሰች ንዋያተ ቅዱሳኑን እየዘረፈች ወደ አክሱም ተቃረበች፡፡ ይህንን ያዩ አባቶች ታቦተ ፀዬንን ይዘው ሸሹ፡፡ ዮዲትም አክሱምን ከበረበረች በኃላ ታቦተ ጽዬንን ይዘው የሸሹትን ፍለጋ ማሳደድ ጀመረች፡፡ አባቶችም ብዙ ተጉዘው ዝዋይ ቢደርሱ ባህሩ ወሰን የሌለው ሆኖ አገኙት፡፡ ወደያውም ከዳርቻው ላይ ከተቆረሰ መሬት ላይ ወጥተው ወደ ታላቅ የሆነው ተራራ (ደብረ ጽዬን) ገቡ፡፡ (ዛሬ ላይ ቦታው ቱሉ ጉዱ ይባላል፡፡) ታቦተ ጽዮንንም ማሳረፊያ ቦታ ሲፈልጉ በእሳት ምልክትነት ያምኑ ነበርና እሳት የወጣልን ቦታ እናሳርፋታለን ብለው ሁለት ቦታ ሲሞክሩ አልወጣ አላቸው፡፡

በሶስተኛ ጊዜ ሲሞክሩ ከተራራው አናት ላይ እሳት ወጣላቸውና ዋሻ ፈልፍለው ታቦተ ጽዩንን የሰደቱ ዘመን እስኪያልፍ አስቀምጠው ጠበቋት» ብለዋል::[6]

ከላይ ካለው የጥበብ ሰዎች ታሪክ ጋር የእሳት አምልኮው ጉዳይ መጋጠሙና የጥበብ ሰዎች መሃል አንዱ ኢትዮጵያዊ ነው የሚለውን መፀሀፍ ቅዱሳዊ መረጃ የሚያጠናክር ያደርጋዋል:: በታሪካዊው ትንታኔ ለሚመለከተው ደግሞ በዮዲት ጉዲት ወረራ ወቅት ማለትም ከ 10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ክርስትናን በቀጡ ሊረዳ የሚያስቸለው የመስፋፋት ደረጃ ላይ በመሆኑ በአክሱምና በሰሜን ሸዋ ድረስ በእሳት የሚያመልኩ መኖራቸውን የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም::

ሁሉም ሰው እንደሚያውቀው ግን ኢትዬጵያውያን በመስቀል በአል ወቅት እንደሚደረገው ክብረ በአሉ ላይ ችቦን በማንደድና እጣን በመጨመር መስቀሉ የመገኘቱን ታሪክ አርአያ በማድረግ ተመሳሳይ ሥራ እነኝህ የጥንቱ አባቶች ሰርተው እንደነበር ወይም ሌላ መጠናትና መመርመር ያለበት የታሪክ ክፍል ያደረገዋል:: የቅድስት እሌኒ የመስቀሉን ማግኘት ታሪክ በአብዛኛው የሚታወቅና በየአመቱ አብነትዋን ህዝቡ የሚደግመው በመሆኑ እርስዋም ደመራን የመደመርዋን እሳት ለኩሳ እጣን የመጨመርዋን ከዚህም በኋላ እጣኑም መስቀሉ የተሰወረበትን ተራራ የጠቆመበትን ታሪክ መሆኑን



የሚያውቀው አማኝ የታቦተ ጽዩንን ማርፊያ በዚያው ሥርአት ፈልገው ነበር የሚሰኘው ሀሳብ ይበልጥ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርገዋል::

የከርሰ ምድር ቁፋሮ ካስገኛቸው ተጨባጭ የታሪክ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት ብቻ ከሆነ ብዙ ጊዜ ከሚታወቀው የድንጋይ ላይ ፀሁፍ በመነሳት ክርስትና በኢትዮጵያ ምድር የመሰበክ ነገር «ሀ» ብሎ የሚጀምረው ከአብርሃ ወ አጽብሃ የመጠመቅና የከሳቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ ዘ ኢትዬጵያ ሊቀ ጳጳስ መስኘት ጋር የተያያዘ ሆኖ ብቻ ነው:: ነገር ግን ከዚህ በፊት ክርስትና በኢትዮጵያ ህዝብ ጉያ ውስጥ መኖርዋን የሚያሳዩ ብዙ የታሪክ ፀሃፊዎች ግኝትን መመልከት ጉዳዩን በይበልጥ ያብራራዋል::

ከነዚህም መሃል ዶ/ር ትርሚንግሃም «ክርስትና በአክሱም ውስጥ ከባይዛንቲዩም (ቁስጥንጥንያ) ጋር ባለው የባህርና የንግድ ግንኙነት ምክንያት ቀደም ባለ ጊዜ ውስጥ እንደገባ ይታወቃል» ብለዋል:: [7]

በተመሳሳይ መልኩ ኘሮፌሰር ታደሰ በበኩላቸው የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የአክሱም ንጉስ የነበረውን የዞስካለስን የግሪክ (በፅርእ ቋንቋ) እውቀትና የንግድ ግብይት ብልህነት ቅርብ ከነበሩ በዘመኑም ክርስትናን ከተቀበሉ የግሪክ ሰዎችና እንዲሁም አማካሪዎች በአክሱም ታላላቅ የወደብና የንግድ ከተሞች ውስጥ ተቀምጠው በሚያደርጉት ሥራ

የተስፋፋ እንደነበረ ግልጽ ነው ካሉ በኋላም የአብርሃ ወደ ክርስትና ሃይማኖት መግባት የተገኘው ህዝብ ቀስ በቀስ ወደ ክርስትና መግባት ባስከተለው መጠናከር እንዲሁም የሮማውና የቁስጥንጥንያው የንግድና የባህር ጉዞ የውጭ ግንኙነት ካለው ተፅእኖ እና የአክሱሙ አጋር ሀገር የቁስጥንጥንያው መንግሥት ሙሉ በሙሉ ክርስቲያናዊ መንግስት መሆን ጋር የተይያዞ የመምጣት ሂደት ነው ሲሉ ይደመድማሉ:: [8]

በተያያዥ የኢትዮጵያን ክርስትና ያጠኑ ሌሎች የታሪክ ፀሀፊዎችም ክርስትና በኢትዮጵያ ጥንታዊነቱ ከአጼ አብርሃ የቀደመ ስለ መሆኑ ይስማማሉ:: ጥንታዊ ከሆኑ የታሪክ ፀሀፊዎቸን ስንመለከት ደግሞ ይህ ጉዳይ ይበልጥ እየጠነከረ የማያጠያይቅ ሀቅ የሚያደርገው መሆኑን መረዳት ይቻላል::

ለዚህም ፕሮፌሰር ስርገው እንዳደረጉት ምርምር ጥንታዊያን (በዘመኑ የነበሩ) (Contemporary) የታሪክ ፀሀፊዎች አበውን በዚሁ ሃሳብ ላይ ይጠቅሳሉ:: ለምሳሌም ያህል ኦሪጅን (origen) እንደፃፈው «ወንጌል በመላዋ ኢትዮጵያ አልተሰበከም በይበልጥ ከወንዙ ማዶ ለሚኖሩት አልተሰበከም» ይላል:: እንደ የቤተ ክርስታያን ታሪክ ፀሀፊ ሩፊኖስ በተጨማሪም ሶክራተስ ደግሞ «ሐዋሪያት ወጌልን ለመስበክ እጣ ሲጣጣሉ ቅዱስ ማቴዎስ ኢትዮጵያን እንዲሰብክ እጣ ደርሶታል:: በዚያም ሐዋርያዊ ተልእኮ ስማእትነት በኢትዮጵያ ተቀብሎአል» ብለው የፃፉት ይገኛል:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ



አባት በመባል የሚታወቀው አውሳቤዎስ «ጃንደርባው ለወገኖቹ ሐዋሪያ ሆነ» ሲል የመጀመሪያውንና ጥንታዊውን እንዲሁም መጽሀፍ ቅዱሳዊውን መረጃ ያጠናክራል ዮሐንስ አፈወርቅ በጥቅምት እለት በሚነበበው ድርሰቱ ላይ «ኢትዮጵያውያኑም ሰምተው ተረዱ» ሲል በሐዋርያት ሥራ ም2 ቁጥር 1 ያለውን የመንፈስ ቅዱስ መውረድና ልሳናት ለሐዋርያት መገለጥ አያይዞ የኢትዩጵያውያን በቦታው መገኘትና ማመንን ያመጣል:: እንዲሁም «የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሐዋሪያ ቅዱስ ቶማስ ነው በማለት ይዘግበዋል:: አባ ጀሮም ደግሞ ቅዱስ እንድሪያስ ነው» በማለት ሌላ መረጃ ይሰጣሉ::

ፕሮፌሰር ስርገው ሲያስረዱ ገና በ1ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የክርስቲያን ማህበራት የነበሩና እነኚህም የጃንደረባው ስብከት ፍሬና በርሱ ስራ ላይ የግሪክ ክርስቲያን ነጋዴዎች አገልግሎት የተደመረበት እንደ ነበረ ይጠቁማሉ [9]

በመፀሀፍ ቅዱስ የወንጌል ምንባብ ላይ ትኩረት ሰጥተን እንድምታዊ ትርጓሜን ካጠናን ስለ የጌታችን ልደት ሁናቴ በሥፋት ከፃፉት መካከል የቅዱስ ማቴዎስን እና የቅዱስ ሉቃስን ወንጌል እናገኛለን:: ቅዱስ ማቴዎስ የወንጌሉን መጀመሪያ በማቴዎስ ምዕራፍ 1 ላይ «የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መፀሐፍ» በማለት ይከፍታል:: ይህም ዋናው ምክንያት ትንቢት የተነገረለት

ሱባኤ የተቆጠረለት የዘመነ ፍዳ አሳላፊዋ የዘመነ ምህረት ሰጭዋ ጌታ መድሐኒአለም እርሱ ክርስቶስ የመወለዱን ዘመን ለመንገር ነው፡፡ አንድም አዲስ ዘመን ወይም ዘመነ ምህረት ሆኖአልና ሲል ሰው ሁሉ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አንድ ብሎ እንዲቆጥር ነው፡፡ ይህም በምን ይታወቃል ቢሉ አብርሃም ለኪዳነ ኦሪት መስረት ነው፡፡ ጌታችን ደግሞ ለኪዳነ ሀዲስ ሰጭዋ ስለሆነ ሁለቱ ዘመኖች መገለጣቸውን ለማጠየቅ «የአብርሃም ልጅ» ብሎ አመጣው ማለት ነው፡፡

ቅዱስ ማቴዎስ ስለዚህ በሰበከበት ቦታ ሁሉ ዘመኑን አንድ ብሎ የ5500 ዘመን ህልፈትን ተረድቶ እንዲቆጠር ያስተምራል፡፡ ከላይ ባየነው መሠረት ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ሰብኮባቸዋል ከተባሉት ቦታዎች አንዷ ኢትዮጵያ ናት፡፡ ስለዚህ የጌታን ልደት እንድንረዳ እና ክርስቲያናዊ ዘመን መቁጠሪያ እንዲኖረን ምክንያት ሆኖአል ማለት እንችላለን፡፡[10]

ቅዱስ ሉቃስም ስለ ጌታ ልደት ወራቱን በብርዳማው ጊዜ መሆኑን ዘመኑን ደግሞ በነገስታቱ ቄሬኔዎስ በሶሪያ ደጅዝማች በተባለበትና ሰው የሚቆጠርበት ትእዛዝ ከቄሳር /አክቴቪያን/ በመጣ ጊዜ እያለ ይጽፋል፡፡ ከሌሎቹም መረጃዎች ጋር ስለ ደቡብ ንግስት ሳባ ከጌታ መዋእለ ስብከት ትምህርት ያለውን ታሪክ በወንጌሉ ማቴዎስ ጽፎአል (ማቴዎስ 12:42) ይህንንም ማለቱ እና ስለ ኢትዮጲያ መጥቀሱ ጌታ እምነትዋን እንደመሰከረላት ወደ ሃገርዋ በእምነትም እንደገባች ምግባሯ



ህዝበ እለራኤልን መገሰጽያ እንዳደረገላት ብቻ ሳይሆን በእርሷ ህዝቡንና ሀገሩን መናገር ልማድ ነውና የኢትዮጵያ ሰዎች አምልኮ በኦሪት የመሆኑን ነገር ሊያመለክት ወደ በነቢያት ትንቢት ያልቀረቡትን፣ ዘመኑንም የልተረዱትን የጌታችን ዘመን እስራኤላውያንን የበለጡ መሆናቸውን እንዲሁም በጌታ ዘመን ኢትዮጵያውያን መገለፁን ተረድተው ለማመንም የፈጠኑ መሆኑን የረጋግጣል ለዚህም ነው በወንጌለ ዩሐንስ (20:29) ጌታ «ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው፡፡» ያለው ለኢትዮጵያውያን ነው የሚባለው፡፡[11]

ሌሎች የኢትዮጵያን ክርስትና ያጠኑ ፀሀፊዎችም የክርስትናው ጥንታዊነት ከአፄ አብርሃ የቀደመ ስለመሆኑ ይሰማማሉ፡፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የሜሮዌ ሰው እንጂ አትዮጵያዊ አይደለም በማለት የሚከራከሩ ሌሎች ሰዎች ቢኖሩም የመረጃቸው ተጨባጭነት ግን አይታይም፡፡[12]

ይህንንም የሚያስብለው ሜሮዌ በአይሁድ ሃይማኖት የተጠናከረ ማህበረሰብ ያለው ሰልጣኔ ያለመሆኑ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ወደ እስራኤል /እየሩሳሌም/ ሐይማኖታዊ ጉዞ የሚያደርግና የባህር ወደብ ባለቤት ጭምር ሥልጣኔ አለመሆኑ ነው፡፡[13]

ይልቁንም በኢትዮጵያ ጥንታዊ የኦሪት እና የክርስትና እምነቶች መገኘት ልማዶቹም ሥር የሰደዱ መሆናቸውን ለመረዳት አያደግትም፡፡ መረጃዎቹም በቀላሉ በየቦታው

የሚታዩ ሀቅ ሆነው እናገኛቸዋለን:: ስለሆነም ጃንደረባው ኢትዮጵያዊ ነው ከሚባለው ታሪካዊ እውነት ውጭ የጌታን የልደት አመት እንዲሁ ተገንዝቦ ለሀገሩ ሰዎች ያስተማረ ሐዋሪያ እንደሚያስኘው ለመረዳት አይከብድም ::

ይህ በዚህ እንደለ ትተን ስለ ኢትዮጵያዊው ዘመን አቆጣጠርን አስመልክተው ከፀፋት ጥቂት ኢትዮጵያውያን መከከል እንዳንዶቹ የሚሉትን መመልከት ይጠቅም እንጂ አይከፋም ከአቶ ጌታቸው ስንጀምር ስለ ኢትዩጵያዊው ዘመን አቆጣጠር በፃፈው መፀሀፍ ላይ የዘመን አቆጣጠሩን መጀመርያ ሙሴ በኋላ ሐዋርያት ቀጥሎም ቅዱስ ድሜጥሮስ እንዲሁም አቡሻከር እያቀነባበሩት ወደኛ እንደደረሰ ከገለፀ በኃላ «እኛ ኢትዮጵያውን መቼ ወደኛ እንደመጣነው በትክክል የሚታወቅ ነገር የለም ግን መጀመሪያ እራሳችን የደረስንበት የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት እንደነበረን የሚያሳዩ አንዳንድ ምልክቶች አሉ :: በዚያም ላይ የውጭውን እወቀት በተደጋጋሚ በተለያዩ ዘመን እንዳመጣነው አያጠራጥርም »[14] ሲል የሃሰቡን ምልከታ ይሰጥበታል ሌሎች ይህንን ጥያቄ በሥፋት የልዳሰሱት ሆኖ የቀረበትም ሁኔታ አለ::[15]

የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ልዩ የሚደርገው ሌላው ክፍል አመቱን በአራት ወቅቶች የመክፈሉና እነዚህም ወቅቶች በቀን ሳይቀር የተከፋፈሉ መሆናቸውን በጥሞና ሰው እንዲያስተውለው አስገነዝባለሁ::



በዚህም መረጃ በብሉይ ዘመን የነበረው አቆጣጠራችን ኢትዮጵያዊ የሚያሰኘው እንደሆነ እንረዳለን:: ይህ ደግሞ ከዘመነ ሐዲስ በፊት ስለ አለው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የራሳችንና ምንጬም ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚነሳ በጣም ጥንታዊ ዘመን መቁጠሪያ ሥርአትና አቆጣጠር እንደሆነ እንረዳለን:: አንባቢያን ልብ ሊሉ የሚገባቸው ነጥብ ቢኖር በዚህ ስራ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ዘመነ ብሉይን የማይጠቀልል በዘመነ ሀዲስ ብቻ ላይ የተደረገ ጥናት የመሆኑን ነገር ነው:: በዘመነ ሥጋዌ በግብፀ እስክንድርያ በሐዋርያው ማርቆስ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በቅዱስ ድሜጥሮስ ከዚያም በቅዱስ አትናቴዎስ አማካኝነት ለኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ቀቢነትና ሿሚነት የተቀበልነው እንደሆነ መረዳት እና የዘመኖቹን ክፍፍል ማጤን ያስፈልጋል::

ከዚህ በተለየ መልኩ አወሮፖውያኑ (እንግሊዛውያኑ) በቢ.ቢ.ሲ. የኢትዮጵያን አስራ ምእት ዘገባ) ስለ ጉዳዩ አፋቸውን ሞልተው እንደተናገሩት «የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የመነጨው በ42 ቅድመ ልደተ. ክርስቶስ በነበረው በጁሊየስ ቄሳር ትእዛዝ የወጣውን ዘመን መቁጠሪያና አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ በተወሰነው ውሳኔ የተቀበሉት ሲሆን አሁን ካለው ጎርጎሪያዊ ዘመን ጋር ልዩነቱ ከዚህ የተነሳ የመጣ ነው::» ብለዋል::

«ከዚህም ውጭ የአስራ ምእቱ በአል ለዳንሰና ለፈንጠዝያ ሰበብ እንጂ እወነታኛው አሥራ ምእት ከተከበረ ሰምንት አመት አልፎታል:: ብለውም ነበር:: ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ኢትዮጵያዊውን ዘመን አቆጣጠር ለማንቋሸሽ ብሎም እኛ ትክክለኛ ነን በሚል ከንቱ የኩራት መንፈስ የመነጨ ባዶ ጩኸትን የማሰተጋባቱ ጉዳይ ስለሆነ በተገቢው ቦታ የዚህን ሀሳብ ምንነትና ስህተት ለይተን ለማየት ወደሚያስችል ምእራፍ ላይ እስክንደርስ ድረስ እናቆየዋለን::



## <u>የምእራፍ ሁለት</u>

## <u>ማገናዘቢያ ጥቅሶች</u>

1. James Breasted, ( PH.D) **Ancient Times : A History of the Early world.** (Boston, 1916) P.46
2. የሐዋርያት ሥራ 8:1-4 ፣የሐዋ 2:13፣ማቴ 28:16
3. በሐዋርያት ሥራ 8:39 ላይ የተጠቀሰው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በ34 ዓ.ም እንዴት ይጠመቃል ቢሉ ነገሩ የሚፈታው የጌታችን እድሜ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ 33 ዓመት ከ 3 ወር በመሆኑ በ34 ዓ.ም እያለ ከሚለው በመነሳት ነው:: በአመቱ ለስግደት ጃንደረባው ወጥቶ ከሆነ በ35 ዓ.ም ይሆናል:: እንደ ኦሪቱ ትእዛዝ መሠረት በአመት ወደ ኢየሩሳሌም መውጣት ህግ ነበርና በ34 አመት የመጣ ከሆነ ደግሞ ከ34 ዓ.ም ተጠምቋል በሚል አመቱን የተረዳነው ነው:: ክቡር ተክለ ጻድቅ መኩሪያ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጉዬ</u> /አዲስ አበባ፣1966 ዓ.ም/ ገጽ 252 ተመልከት
4. ሚኒሊክ መርእድ አለሙ፣<u>መጸሐፍ ቅዱስና ኢትዮጵያ</u> (አዲስ አበባ፣1999 ዓ.ም ) ገጽ65-110
   ይኸው መጸሐፍ ላይ በስፋት ይህንን ጉዳይ ያብራራዋል:: ይልቁንም ማስረጃዎቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በመሆናቸው ትውፊቱን በመረጃ ያጠናከረውና

ያበለፀገው ስለሆነ በጣሙን «ይበል» የሚያሰኝ ሥራ ያደርገዋል:: እንደ አንድምታው ትርጓሜ (ዘ ማቴዎስ) የሰብአ ሰገል ነገስታት ስም ማንቱሲማር፣ ሜልኩ ፣ በድድ አስፋ ይባላል:: በድድአስፋ ምስራቃዊ ስም ሳይሆን የዛጉዬ ነገሥታት በኃላኛው ጊዜ የሚሰየሙበት ጋር ይመስላል የሚሉ ማመልከቻዎች ሲሰነዘሩ ኖረዋል::

5. ይህ ገፀ ንባብ በአንድምታ ወንጌል ዘማቴዎስ ያለ ቢሆንም በስፋትና ጥልቀት ለማየት ተአምረ ኢየሱስ /ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ማተሚያ ቤት 1990ዓ.ም/ 7ኛ ተአምር ገፅ 28-33 ያለውን ተመልከት::

6. <u>የካቲት 1997 ፀሀፊው ከደብረ ጽዮን ማርያም አስተዳዳሪ</u> ጋር ያደረገው ውይይት ስለ ቦታው ገለፃ ላይ የሚያስታውሰውን ከዚህ ፀሁፍ ላይ ገልፃል::

7. See, J. Trimingthm, **Islam in Ethiopia** ( London. ,1952) P. 38 ይህንን መፀሀፍ መመልከት ያሻል ነገር ግን በውስጡ ስለተካተቱት ነጥቦች በኃላ ወሳኝ አስተየየት ይሰጥበታል::

8. See, Professor Taddesse Tamrat, **Church and State in Ethiopia 1270-1527** (Oxford, 1972) P.21



9. See; Triningham; p. 38 specially footnote 1; Professor Sergew Hable Sellassie, **Ancient and medievial Ethiopian History to 1270** ( Addis Ababa, 1972) P.97

10. See; Trimingham. P.38 the footnote indicates that according to Socrates and Ruffinos. Mathew preached in Ethiopia. በዚህ መረጃ ላይ ሁለት ታሪክ ፀሀፊዎች አንድ ቅዱስ ሐዋርያን ማንሳታቸው ለነገሩ ትኩረት የሚያሰጠው ያደርገዋል::

11. እንደ ቤተክርስቲያን ትምህርት በእስራኤል የነበሩ አይሁድ ጌታ በእጁ ገቢረ ተአምራት እየሰራ በአፉም ሌላ ሰው ያላስተማራቸውን ትምህርት እያስተማረ ቢሰብካቸው ስላልተቀበሉት ትንቢትና ነብዮችም ሁሉ ወደ እነርሱ እየተላኩ አምላካቸውንም በዓይን አይተው ያላመኑት የኦሪት ልጆች ሲያደርጋቸው በአለም ላይ ከእስራኤላውያን ውጪ ኦሪትን ለመቀበል እና የእግዚአብሔር ህዝብ ለመባል ከጣኦት አምልኮም ለመውጣት የፈጠኑ ኢትዮጵያውያን ኦሪትን ከወንጌል ጋር አስተባብረው በሰዓቱ የጌታን ፊት ሳያዩ እና ገቢረ ታምራቱን ሳይመለከቱ በመቀበላቸው ብፁአን ይሰኛሉ የሚል ትምህርት አለ::

12. ይህንን ጄ. ኤስ. ትሪሚንግሀም እስልምና በኢትዮጵያ (ለንደን 1952) ገፅ 38 ከማገናዘቢያ ጥቅስ ቁጥር 1 ላይ

የፃፉት ሲሆን ፕሮፌሰር ሰርገው <u>በጥንታዊውና መካከለኛው የኢትዮጵያ ታሪክ</u> መፅሀፋቸው ገፀ 97 ምላሹን ከፀሁፉ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ያስቀምጡታል፡፡

13. See; Professor Sergew, p.97

14. አቶ ጌታቸው ኃይሌ <u>ባሕረ ሐሳብ የዘመን አቆጣጠር ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋር</u> (ኮሌጅቪል ሚኒሶታ፣ 1993 ዓ.ም) ገፀ 19 የአቶ ጌታቸው ሀሳብ ላይ "የኛ" ከጥንት አባቶቻችን ያገኘነው እና ሊቀ ነብያት ሙሴ፣ሐዋርያው ቅዱስ ድሜጥሮስ እያለ የሚመጣው ዘመን አቆጣጠር በማለት የለየው ይመስላል የኛ ጥንታዊ ዘመን አቆጣጠር የተባለው ግን ምን እንደሆነ ምንም ፍንጭ አልሰጠም ይልቁንም ከጥንት ከሊቀ ነብያት ሙሴ እስከ አሁን ድረስ ያለውን በአግባቡ ጠብቆ መያዝ በራሱ የኛ ሊያስብለው ይገባል ወደሚል ሃሳብ መምጣት ተገቢ ነው ለምሳሌም እንደ መጽሀፈ ሄኖክ ለማለት ተፈልጎ ነው አለበለዚያ የኛ ስለተባለው ጉዳይ ግልፀ ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

15. ሊቁ ፕሮፌሰር ሰርገው ስለዚህ ጉዳይ ሲያስረዱ የጠቀሱት የሁለት የዘመን አቆጣጠር ጠበብት ሐሳብን ነው፡፡ ይህም ጁልያን አፍሪካዊ የሚባል በ221 አመተ እግዚእ አለም ከተፈጠረ 5500 ዘመን ላይ ጌታ ተወለደ



ሲል መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን አበው እድሜ ደምሮ እጌታ ላይ ደረሰበት ሌላኛው ደግሞ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሳ ፓንዶር የተሰኘ ሰው የአለም እድሜ 5,492-3 ነው በማለት ካሳወቀው የተነሳ ልዩነቱ 7 እና 8 አመት ቅድመ ልደት ሲመጣ የኢትዮጵያው በጁልያን የጌታ ልደት 1 ዓመት በፓንዶር ደግሞ በ7 ዓመተ እግዚእ ነው ያለውን ተከትሎ በኛና በአወሮፓ መካከል ልዩነት አለ ሲሉ ቢያስረዱም አውሮፖውያኑ ከላይ የተጠቀሰውን የፖንዶርን ትምህርት ስለ መቀበላቸው የሚታወቅ ነገር የለም ይልቁንም የዘመን መቁጠሪያቸውን ምስረታ የሚጠሩት ከዲዮናሲዮስ ኤክሲጆስ በመሆኑ ይህ ምልከታ ግልጽ ያልሆነ ክፍል ሆኖ የቀረበ ይሆናል? ነገር ግን እንደዚህ ሆኖ የቀረበ ይሁን እንጂ ከዚህች ምልከታ በቀር ልዩነቱን በግልፅና በሰፊው የዳሰሰ ስራ ምንም አልተገኘም በዚህ ፀሁፍ ውስጥ የጁሊያን አፍሪካዊ ሀሳብ የሚለውን ከየጁልያን «ካላንደር» ከሚባለው ጋር ያለውን ልዩነት አስተውል፡፡

# ምእራፍ ሶስት

## የግብጽ (ቅብጥ) ቤተክርስቲያን ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙት

በጥንት ጊዜ ግብፃውያኑ ዘመን አቆጣጠርን ከዋክብትን በመቁጠር ጀምረውት ነበር ይህንንም አምስት አለማትን (planets) ሠላሳ ስድስት ከዋክብትን ለቆጠራ በመለየት ለምርምራቸው መነሻና መወሰኛ የዘመኑን ማመላከቻና የማገናዘቢያ ነጥቦች አድርገዋቸዋል:: የጥንቱ ግብፃውያን ስለ ኮከብ ቆጠራ ስለ ወቅት ስለ የአመቱ ቀናት መጨነቃቸውና መጠበባቸው እንዲሁ ለከንቱ አልነበረም:: በበረሃው ሀገራቸው የወቅት መፈራረቅ ከዝናብና ከልምላሜ ጋር ወይም ደግሞ ሙቀትና በጋ ከደመናና ከቅዝቃዜ ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከአባይ መሙላት ጋር የተዛመደ በመሆኑ እንጂ:: ስለሆነም አባይ ድንገት ሞልቶ በሚፈጥረው ደለል ምርትን ለማምረት ወይም ንብረትን ለማዳን አስቀድሞ ክረምት የሚገባበትን ወቅት ጠንቅቆ ማወቅ ይገባ ስለነበር ነው:: ከዚያም አልፈው የውሃውን ጥልቀት በየጊዜው በመለካት ቀስ በቀስ እየደገ መሄዱንና አለመሄዱን ያጤኑም እንደነበር ዛሬ ላይ በጥናት ታወቋል:: ይህንን ሁሉ ከ2776



ቅ.ል.ክ. በፊት እንዳከናወኑት በአንዳንድ መረጃዎች ላይ ይወሳል::

በግብፃውያን የዘመን አቆጣጠር መስረት 365 1/4 ቀናቶች አመቱ የተከፋፈለ ሲሆን ይህም በፀሀይ ኡደት ከመቁጠር የመጣ መሆኑ በታሪክ ይታወቃል አመቱም በወራቶች የተከፋፈለ ሲሆን ይህም በ12 ወራቶች እያንዳቸው ሰላሳ ቀን ያላቸው እንዲሆኑ ተደርገዋል:: ቀሪዎቹ አምስት ቀኖች እራስቸውን የቻለ ወር የተሰራላቸው ናቸው:: ይህም በዘመኑ ከነበሩት በጨረቃ ኡደት ከተመሰረቱ የዘመን መቁጠሪያዎች በጣሙን እርቆ የቀደመና የመጠቀ ዘመናዊ እና ተግባራዊ የሆነ ዘመን መቁጠርያ የደርገዋል::[1]

ይህ ታዲያ እንደሚያመለክተን ጥንታዊ ሥልጣኔ ከተነሳባቸው ከግብፅ፣ ከሜሶጶጣሚያ፣ ከህንድ፣ ከቻይና እና ከኢትዮጵያ ውጭ ድፈን አውሮፓና ሌሎቹም ገና በየዋሻው እንደ አውሬ በሚንፏቀቁበት የእውቀትንና የትምህርት ብሎም የዘመኑን የጊዜውንም ሁናቴ ለመመርመር በማይቻሉበት የሥልተ ምርት ሁናቴ እና ሥልጣኔ ውስጥ የነበሩ መሆናቸውን እንድንገነዘብ ያደርገናል:: እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ አንድ ስልጡን ህዝብ ለሌላ ስልጡን ህዝብ ሥልጣኔውን እያቀበለ ከሚያወርስው ታሪካዊ ሂደት ውጭ ከየዋሻው እና ከደን ውስጥ መንደሮች ብሎም ከየረግረጉ እንደ ከርከሮ ከመኖር የመጡት የአውሮፓ ዘላናዊ ጉሳዎቸ ምንም አይነት

የዘመን አቆጣጠር ቀመር ለነዚሁ ሀገሮች የማዉረስ ብቃት የሌላቸው መሆኑንም እንድናጤን ያደርገናል፡፡ ዛሬ ዛሬ ታሪኩን ጠንቅቆ በማያወቀው ወጣትና ብሎም ባለው አንፃራዊ የአለም የምጣኔ ሀብት ብልጫና ልዩነት በመጠቀም አውሮፓውያን ብሎም ሰሜን አሜሪካ በስልጣኔ ጥንትም ገናና እንደነበሩ ለማስመሰል የሚያደርጉት የባህል ወራራ ምነኛ አስቀያሚና አስነዋሪ ድርጊት መሆኑንም እንረዳበታለን፡፡ በይበልጥ ይህ ደግሞ «የአውሮፓ ዘመን መቁጠሪያ አለም አቀፍ ይሁን እና ከኛ ዘመን መቁጠሪያ ውጭ ሌላው ሁሉ ካልጠፋ» በማለት በማን አለብኝነት የሚያዘሩትን ሁከት ለሚያስተውለው ሁሉ ምንኛ ትዝብት ውስጥ ይጥላቸው ይሆን ?

በተያያዥ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠርን አጀማመር የሚገልፁ ታሪካዊ ትችቶች እንደሚያስረዱት ኢትዮጵያውያን ያላቸው የዘመን አቆጣጠር አጀማመሩ ከሄኖክ መፀሀፍ አንድምታዊ ትንታኔ የተወጣጣ ውርስ ነው የመባሉ ነገር ነው፡፡ በመፀሀፈ ሄኖክ ላይ ቅዱስ ሄኖክ በሰፋት ስለ ከዋክብት እና የአመት ወቅቶች፣ስለሚወጡበት እና ስለሚገቡበት የሰማይ መስኮት፣ ስለ ኡደታቸው ሁሉ አንድ በአንድ ይዘረዝራል፡፡ ይህንንም የሰማይ ሥርአት የሥርአቱም መጋቤ መላእክትንም ስም ወደ ስማይ ተነጥቆ እንደጉበኝና ጥልቅ የሆኑ ሚስጠራትን እንደተረዳ ይገልፅልናል፡፡ እነዚህም በጥቂቱ ከተወሰዱ ጥቅሶች ስናያቸው ይህንን ይመስላሉ፡፡



መፀሀፈ ሄኖክ 21:1-መጨረሻ «ስለ ፀሀይ ኡደት ቁጥር 6 ላይ ፀሀይ የሚወጣባቸውን ስድስት መስኮቶችን አየሁ፡፡ ፀሐይ ከሚገባባቸው ቦታዎች 6 መስኮቶችንም አየሁ፡፡ ጨረቃም በነዚያ መስኮቶች ይወጣል ይገባል፡፡ ቁጥር 9 ላይ በዚያም መስኮት በግራና በቀኝ ብዙ መስኮቶች አሉ (ሚያዝያ ነው) ቁጥር 17 ላይ በነዚያም ወራት እስከ ሠላሳ ቀን ድረስ ቀኒቱ ከቀን ትረዝማለች ሌሊቱም ከሌሊቱ ታጥራለች በቁጥር 18 ላይ በዚያችም ቀን ቀኒቱ ከለሊቱ ሁለት እጅ ትበልጣለች ጠንቅቀው ቢቆጥሯት ቀኒቱ አሥር ክፍል ትሆናለች ሌሊቱም ስምንት ክፍል ትሆናልች፡፡

ቁጥር 23 ላይ «ፀሀይም ወደ ምሥራቅ ይመለሳል ወደ ስድስተኛይቱም ደጃፍ ይገባል የጳጉሜ ቀን ከሷ ጋር ስለ ኖረች በስድስተኛይቱ ደጃፍ ሠላሳ አንድ ቀን ይወጣል ይገባል በዚያችም ቀን ቀኒቱ ከሌሊቱ ትረዝማለች ቀኒቱም የሌሊቱ እጥፉ ትሆናለች ቀኒቱም አሥራ ሁለት ክፍልን ትሆናለች ሌሊቲቱም አስራ ስድስት ክፍልን ትሆናልች» (ስኔ) ምእራፍ 22 ቁጥር 1 «የዚህን የፀሀይ ሥርአት ካየሁ በኋላ ስሙ ጨረቃ የሚባል የታናሹን ብርሃን ሌላ ስርአት አየሁ ... ሁለተኛ መሄጃውን ሁለተኛ ትእዛዙንም አየሁለት» ይላል፡፡ ምእራፍ 24 ቁጥር 1 «በፍጥረቶቹ ሁሉ ላይ በኮከቦቸም ሁሉ የተሾሙ የሺህ አለቆች የሚመሯቸው የወር መጋቢዎችን

የሚመሩ የ91 መጋቢዎች በዚያ ይወጣሉ::» እያለ ጥልቅ የሆኑትን ሚስጢራትን ይዘረዝራል::

ይህ መፅሀፍና ትምህርቱ እጅግ ጥንታዊ ከመሆኑ የተነሳ የተፃፈው በዚህ ጊዜ ነው ለማለት ያስቸግራል:: በመሆኑም የመጽሀፉ ኢትዮጵያ ውስጥ መገኘትና ስለ የከዋክብት ሂደት እና የወቅቶች የጊዜና የወር ቀመር ስለአለው የቤተ ክርስቲያን ዘመን አቆጣጠር ሥርአትን በማጥናት የመጀመሪያው ጥንታዊና ልዩ ኢትዮጵያዊ ዘመን ማቁጠሪያ ዘዴና ትምህርት እንዲሁም መንደርደሪያ መሆኑ በቤተ-ክርስታያን አበው ዘንድ እና በአፋአዊ ትውፊት ይነገራል::[2]

ከዚህ የምንረዳው ነገር ቢኖር ስለ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሰው ለማስረዳት ከተነሳ ዘመን አቆጣጠሩን በሁለት ታላላቅ ክፍሎች መክፈል ያስፈልጋል ይህንንም በብሉይ ኪዳን ጊዜ እና በሀዲስ ኪዳን በማለት በሁለት ታላላቅ ክፍሎች መክፈል ያስፈልጋል:: በዚህም የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ምንጩ መፀሀፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት እንችላለን::

ከላይ ያየናቸው ክፍሎች ሥርአት ባለው መልክ ስንተነትናቸው ዘመን አቆጣጠሩ ጥንታዊነት ከመፀሀፈ ሄኖክ ሲነሳ ኪዳነ አደምን ያጠቃልላል ከዚህ ጋር መፀሀፈ ኩፋሌ እንዲሁም ኦሪት ዘፍጥረትን ከእስራኤላውያን ጋር እኩል እየቆጠርን በ5500 ዘመን የመጣበትን ሂደት ማስተዋል ይገባል ከመፅሀፈ ሄኖክ ውጭ ኩፋሌ ላይ ያለውን አዳም



የተቀበለውን ቃል ኪዳን ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ አድንሃለሁ የሚለው ቃል ይህም የሚፈታው በ2ኛ ጴጥሮስ ም3 ቁጥር 8 ያለው ጥቅስ ሲሆን በዚህም አንድ ቀን አንድ ሺህ አመት እንደሆነ የሰረዳናል::

የዲያቆን በእምነት ምትኩ መጽሐፍ ይህንን በማብራራት እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ ይበል እጅጉንም ይበል የሚያሰኝ ስራ ነው:: ስራውንም ለወደፊቱ በይበልጥ አጠናክሮ ታሪክን ጨምሮ የእዝራ ሱቱኤልንም ቀመር ጠንቅቆ ቢያቀርበው ባሕረ ሐሳቡንም በይበልጥ አስፋፍቶና አጥልቆ ከባዱን ለኛ በሚገባን ቋንቋ እየፈታና የእያንዳንዱን ቃል መሠረታዊ ትርጉም እንደሚያብራራ ተስፋ አደርገለሁ:: ስለ የኢትዮጵያም ዘመን አቆጣጠር በተሰሩ ስራዎች ይህ የበለጠ መረጃ የሚሰጥ ሆኖ አግኝቸዋለሁ:: ለወደፊትም የተሻለ ሆኖ ስለ ኢትዮጵያዊው ዘመን አቆጣጠር አጉልብቶ እንዲፅፈው አስተያየቴን ሳልሰጥ ማለፍ አልፈልግም

በተጨማሪም ዘመን አቆጣጠራችን በኦሪት ዘ ፍጥረት ያለውን የዘመነ አበውን እድሜ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 5 ቁጥር 1-30 ያለውን ደምሮ 5500 የሚያመጣ ዘመን አቆጣጠር እንደሆነ መገንዘብ ያሻል:: ይህንን በጣም ከባድና ሰፊ የሆነ የጥናት ክፍል (የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በዘመነ ብሉይ) ለመዳሰስ ጊዜን የሚወስድ ምርምር በአበውና በነብይያት ሱባኤያት ላይ እነዚህም ሱባኤ አዳም ስንበተ ሄኖክ (መፀሀፈ

ሄኖክ ትርጓሜ) ሱበኤ ኤርምያስ ሰንተ ዳንኤል ሀሳበ እዝራ የሚባሉትን የባሕረ ሐሳብ የትምህርት ክፍሎችን በቅጡ ማገናዘብና ማጥናት ያስፈልጋል። ይህንንም ከጥንታዊውና ከረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ጋር በማስተባበር ታላቅ የሆነ ድርሰትን መፀፍ ያስችላል[3]

ከዚህ ጋር ተያይዞ በዘመነ ሀዲስም የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር እንዲሁ ጥልቅ የሆነ ብዙ ምንጭቸ ያሉት በመሆኑ ሁሉንም መርምሮም ወጥ የሆነ ሥራን ማበርከት ለዚህ ትውልድ የተሰጠ ሃላፊነት ይመስላል። እነዚህም እንደ ወቅያኖስ የሰፋ (በእውነትም ባሕረ ሐሳብ) የዘመን አቆጣጠራቸንን ሊያስገነዝቡ የሚችሉትን ምንጮች በስርአት ብዙ ዘመን የሚያጠና ሰው በአሁኑ ሰአት በጣም አስፈላጊ ነው። ምንጭቹም አቡሻከር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቅዱስ ኤጳፋንዬስ ዘ ቆጳሮስ ቅዱስ ቄርሎስ ዘ እስክንድርያ ሳዊሮስ ዘ ዕስሙናይ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ እና ሌሎችም ታላላቅ ሥራዎችን መመልከት ግድ ነው።

ይህ ስራ በጥልቀት የሚያውጠነጥነው በወሳኝ መረጃዎችና በይበልጥ ደግሞ በዘመነ ሀዲስ ያለውን የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ላይ ሲሆን አላማው ደግሞ ዘመን አቆጣጠራችን ከትክክለኛውና እውነተኛው የጌታ ልደት ዘመን የሚነሳ መሆኑን የማረጋገጥ ይዘት ብቻ አለው ።



የግብፅ ዘመን አቆጣጠር ጥንታዊና ሰፊ ታሪክ በማሳለፍ ለአወሮፓውያኑ የባህላዊና የጨረቃ ኡደት ላይ የተመሰረተውን በአፈ ታሪክም ላይ የሚያውጠነጥነውን በዋናነት የሮሜ ዘመን አቆጣጠርን እንዲሻሻልና ወደ ሥልጣኔ መዳረሻ እንዲደርስ ያበረከተው ተፀእኖ ወደፊት የምናየው ይሆናል። ስለዚህም የቅብጥ (ግብጽ) ዘመን መቁጠሪያ ከክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ጋር ያለውን ትሥሥር መመልከት ከተነሳንበት አርእስት ጋር ታዛማጅ የደርገዋል።[4] ግብጽ የክርስቶስ የስደት ሀገር ናት /ማቴ 2:1/ ሀዋርያት እና አርድእት ወደ ግብጽ ወርደው ሠብከውባታል። ቅዱስ ማርቆስም መንበሩን በእስክንድርያ በማድረግ እስከሞት ድረስ ወንጌልን እየሰበከ ለክርስትና እና ለቤተ ክርስቲያን በግብጽ መተከል ተጋድሎአል።

እስከ ዛሬ ድረስ የተገኙት የቅብጥ ክርስቲያኖች አባቶቻችን ከሐዋርያት እንዲሁም ከወንጌል መሰረትነት የተማሩትን ትምህርት ይዘው የዘመናትን የምንፋቅና ጉርፍ የአህዛብ የግድያ ፊታና መአበል ተሰቅቀው ሳይክዱና ሳይጠፉ አምላካቸውን የሙጥኝ እንደያዙ ስለመዝለቃቸው መረዳት አያዳግትም። ክርስትና «ሀ» ብሎ በእስክንድርያ ከተሰበከበት ጊዜ አንስቶ ሰማእትነት በአህዛብ እና በሮሜ ቄሳሮች ምክንያት የግብጽ ክርስቲያኖች እፃ ሆና ነበር። በዚህም ሁናቴ በ13 ተኛ ው መቶ ክፍለ ዘመን መንፈስ ቅዱስ ሚስጠራቱን የገለጸለት

አቡሻከር ባሰፋፋው በሕረ ሐሳብ እንደሚገልጸው የዘመን አቆጣጠር ሥርአትን መጀመሪያ ሙሴ በመንፈስ እግዚአብሔር ተመርቶ ሥርአትን እንደሰራ ሌዋውያኑም ያንኑ ቀመር እየተከተሉ የአይሁድ ባእላትን ሲያስሉና ሲያስተምሩ አመቱንም ከፍጥረተ አለም ጀምሮ ሲቆጥሩ ኖረዋል::

በጌታችን በመድሐኒታችን መወለድ ዘመነ ፍዳ በማለፉና አዲስ ኪዳን በመመስረቱ የአዲሱ ጊዜ ብሥራትና የምሥራቹን ቃል ከዘመኑ ጋር እየቆጠሩ ሐዋርያት ደግሞ ለክርስቲያኖች አስረክበዋል:: ከዚህ በኋላ በ(188-230ዓ.ም) በእስክንድሪያ ላይ በመንፈስ ቅዱስ የተሾመው ቅዱስ ድሜጥሮስ መንፈስ ቅዱስ ሀይሉን በህይወቱ ገልፆ አእምሮውን አብርቶ ልቦናውን እና እጅቹን አበረትቶ ብዙ ሚስጢር እንደገልፅ ፣የዘመን አቆጣጠር ቀመርን እንዲሰራ፣ የበአላትን አከባበርን ከአይሁድ ባእላት ጋር እያነፃፀረ በሙሴ ከተቀመጠው ቀመር ጋር ህብረቱንና የሚለየውን የክርስተያን ቀመር አግኝቶአል:: እንዲህ ማድረግ ብቻ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ፃፍ ያለው ዘመን ድረስ ባለው አመታት ውስጥ ባእላቱን እና ዘመናቱን ሁሉ ገልፆ ፅፎታል::

ይህንን ሳስተዋለው ሰው መላው አውሮፖና ፣አለም ሁሉ ገና የወንጌል ጠላት በነበሩበት 2ኛውና 3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ቅዱስ ዲሜጥሮስ ስለ ጌታ ልደት፣ ስለ ዘመን አቆጣጠር፣ ስለ አመተ አለምና፣ ስለ አመተ ፍዳ ወይም ኦሪት



እና አመተ ምህረት እያነፃፀረ መፃፉ የጌታን ልደት ለመረዳት እና በቅጡ ትክክለኛውን አመት ለማወቅ ምን ያህል የቀረበ እንደሆነ አያሳይም ወይ? በማለት ምእራባውያኑን ከባድ ጥያቄ እንድንጠይቅ ያደርገናል::


አባታችን አቡሻከርም የአባታችንን የድሜጥሮስን መንፈሳዊ ፀጋ ከታሪክና ከቀመሩ ጋር አስፍቶ በ13ኛው ክፍለ ዘመን የባሕረ ሐሳብ መጽሀፍትን ጽፎልን እንዳለፈ እንረዳለን:: ክዚህ ጋር የሚዛመድ ታሪካዊ ሂደት ላይ እንደምንመለከተው በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ጳጳሳትን ለኢትዮጵያ በመጀመሪያ ጊዜ የቀቡትና የሾሙት የእስክንድርያ ፓትሪያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ ለአባ ሰለማ ይህንኑ የሀይማኖት ሥርአትና ቀኖና እንዲያስተምሩና ህዝቡ እንዲጠብቀው መንፈሳዊ ትሕዛዝና ትምህርት በመስጠታቸው ከሀዋርያት እና ከግብጽ በቀጥታ እንዲሁም ከሀዋርያነ አበው የተረከብነው የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያናዊውን ዘመን አቆጣጠር ስለ መሆኑ አያጠራጥርም:: አባ ሰለማ የጳጳስነትን ፣ ማእረገ ክህነትን ፣ስለ ከህናት አሻሻም፣ ስለ ዶግማ እና ቀኖና ሥርአት እና ሚስጢር ሲያጠኑ በግብፅ ውስጥ ለብዙ አመታት ተቀምጠዋል::[5]

እዚህ ላይ ግን ግብፆቹ እንደእኛ በአመተ ምህረት፣ እና በልደተ ክርስቶስ ወይም እንደ አውሮፓውያኑ በአመተ እግዚእ አይቆጥሩም:: ይልቁንም እነርሱ በአመተ ሰማእታት

ይቆጥራሉ:: እኛ ደግሞ በአመተ ምህረት እንቆጥራለንና ዘመናቸውም ከዘመናች ለየቅል ነው:: በኛ በኢትዮጵያውያኑ ዛሬ 2000 ዓ.ም ሲሆን በነርሱ ገና 1724 አ.ሰ. ነው ቢሉ ነገሩ እንዲህ ይፈታል::

በፊት እንዳየነው በግብጽ ክርስትና ገና ከመሰበክዋ ሰይጣን እና ልጆቹ ተነስተው ለማጥፋት ተረባረቡ:: ይህ የፈተና ማእበል አንዳች ሳይላላ ቀጥሎ በ277 ዓ.ም ገደማ አሰቃቂ የሚሆን የዲያብሎስ የፈተና ዘመን ተጋረጠ ይህ ወቅት በሮሜ ግዛት ላይ ከተራ ወታደርነት ለቄሳርነት ደርሶ አንባገነን የሆነ ዲዮቅልጢያኖስ የሚባል ሰው የነገሰበት በመሆኑ በአስከፊነቱ የሚታወቅ ነው:: በይበልጥ ግን ዘመኑ «ዘመነ ሰማእታት» በመባል ተወዳዳሪ የሌለው የመከራ፣ የእንግልት እና የስቃ እንዲሁም የሲቃ ዘመን የመሆኑን ነገር በሚገልፀው ሀረግ ይታወቃል:: ይህ ሰው ክርስታያኖችን ከምድረ ገጽ ሊያጠፋ ወዶ ይህ ነው የማይበል እልቂትን ከፈተ፣ በዚህም መከራ በአለም ላይ ካሉት ክርስቲኖች ሁሉ ግብጾች በይበልጥ፣ ተጨነቁ፣ ተጨፈጨፉ፣ አለቁ:: የከፈሉትም ስመአትነት ሊዘከር ሊዘረዘር አይቸልም:: በትንሹ ግምት ከስምንት መቶ ሺህ ሰው በላይ ሰማአትነትን ተቀብሎበታል::[6]






ስእል 1 እንደ ስንክሳሩ ሰይጣን እራሱ ልጄ ሲል የጠራው የዲዮቅልጥያኖስ

ታላቁ ቅዱስ እንጦንስም ከበረሃው በአት ወጥቶ ብዙዎችን አበረታ ብዙ መከራም ተቀበለ:: የዲዮቅሊጢያኖስ ሹማምንቱ ሊገድሉት ሞክረው ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ግን በዚህ ይሞት ዘንድ አልፈቀደምና ሊሞትላቸው አልተቻላቸውም እግዚአብሔርም መሳህቲውን እና አላዊውን ገኘ ያሳፈረው ዘንድ ስአቱ በደረሰ ጊዜ አባታችን ቅዱስ ጊዮርጊስን አስነስቶ ሊነገር በማይቻል የመከራና የሰቆቃ ኑሮ

ኖሮ  የዘመነ ሰማእታትን እሳት በተጋድሎው በፈሰሰው የደም ብዛት አጠፋው፡፡




*ስእል2 የሊቀ ሰማእታት ፋጡነ ረዲኤት ብፀእ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሥእል*

የግብጽ ክርስቲያኖችም ዘመነ ሰማአታት አልፎ ቆስጠንጢኖስ ነግሶ አለም ሰላም የሚሆነው ክርስቲያኖች



ከግበበ ምድር የሚወጡበትን ጊዜ ባዮ ሰአት ተጋድሎአቸው ሊከበርላቸው እና ሊዘከርላቸው ለሚገባቸው ለሰማእታቱ ክብር ሲሉ «አንድ አመት ዘመነ ሰማእታት ካለፈ» በማለት አዲስ የዘመን አቆጣጠርን ህግ ሠሩ፡፡ ይህም ጥፋት የለውም የቅዱሳኑን የሰማእታቱን ተጋድሎ ለመዘከር የፀሎታቸው እና የአማላጅነታቸውን በረከት ለመቀበል ብለው ነውና ያደረጉት፡፡



*ስእል 3 እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ የክርስቲያኖች ኑሮ በሮሜ መንግስት ይህን ይመስል ነበር፡፡*

ስለዚህ ዛሬ በኛ 2000 ዓ.ም ላይ የግብፀ /ቅብጥ/ 1724 ዓ.ሰ. ከሆነ በፊት ያለውን የጋራ አመት ወይም እኩል የቆጠርናቸው

276 ዓመቶች ስንጨምርበት 2000 ዓመት ምህረትን ይሰጣናል:: በዚህም የአትዮጵያና የግብፀ የዘመን ሙቁጠሪያ አንድ ነው ምንጨም ቅብጦቸ አባቶች ሊቀ ጳጳሳቱ በሀዲስ ኪዳን ያወረሱን እነርሱም ከሀዋሪያት የተቀበሉት ያመነጨውም እግዚያብሔር ነው የሚባለው::

ማስረጃ: ዛሬ በግብጽ 1724 አ.ሰ. ነው በእኛ ዛሬ 2000 ዓ.ም ነው:: በ1724 አመተ ሰማእታት ላይ የጋራ የሆነውን ቅድመ አ.ስ. 276 ዓ.ም ሲደመር 2000 ዓ.ም ይሰጣል:: ወይም ከ2000 ዓ.ም ላይ 276 ዓመት ሲቀነስ 1724 አ.ሰ. ይሰጣል::

አንዱና ሌላው ማስረጃ መፀሀፈ ስንክሳር ነው በመጽሀፈ ስንክሳር ላይ መስከረም አንድን ገና ከመግቢያው «ይህ ወር የተባረከ ነው እርሱም የግብፅና የኢትዮጵያ የአመቶች መጀመሪያ ነው» ይላል:: መስከረም በጥንቱ እና በአሁኑ ቱት /ቶት/ በግብፀ ልማድ ወይም ርእስ አወደ አመትም በመባል ይታወቃል:: በአውሮፓውያኑ ይህ ቀን በሴፕቴምበር 11/12 የሚውለው ቀን ነው::

ከዚህ ባሻገር የኛ ዘመን መቁጠሪያ 365 ከ1/4 ቀን ያለው እያንዳንዱ ወር በ30 ቀን የተከፋፈለ 13 ወሮችን የያዘና የመጨረሻዋም 5 ወይም 6 ቀን ያላት 13ኛዋም ወር ጳጉሜን በፀርእ / ግሪክ/ ሽራፊ በሚባል ስም ወር ያለው ነው:: ጳጉሜን የሚል የፀርእ ቃል መግባቱ ከእስክንድር



«ታላቁ» ጀምሮ እስከ ተሎሜ ሥርው መንግስት ማብቃያ ድረስ ግብፅ በጽርእዎች ለመገዛትዋ እና ከዚህ በፊት የተሰየመውን የጥንቱን ቃል የተበረዘበት ሂደት በግብጽ ስለ ነበር ነው:: ይህው በራሱ ከነርሱ እንደወረስነው የሚያመለክት መረጃ ነው:: [7]

ሌላው የኢትዮጵያ ባህረ ሀሳብ የፀሀይ አውድ ነው:: ይህ ማለት የፀሀይ ኡደትን የሚከተል ነው ማለት ነው:: ይሄ ደግሞ በጥንታዊው የግብጽ የዘመን አቆጣጠር ወደ ኃላ ደግሞ የቅዱስ ዲሜጥሮስን የባህረ ሐሳብ ቀመርን የሚያመለክት ውርስ መሆኑን ይገልፃል:: በተቃራኒው ሳባውያን በጨረቃ እያመለኩ በሚኖሩበት በጥንት ጊዜ ጨረቃዋን ስን (sin) ወይም አልሙቃህ (Almuqah) በማለት አማልክት ናት ብለው ይጠሩ ነበር:: ወራቶችንም በጨረቃ ልደት አመቱን የጨረቃ ኡደት አድርገው ዘመኑን ይቆጥሩ ነበር:: (Lunar month and year) ይህ ባህል እና ዘመን መቆጠሪያ ጨረቃን የበድዊኖች (Bedawin) የደቡብ አሬቢያ እና የሳባ ተወላጆች ሁሉ የዘመን መቁጠሪያ እንደሆነ መረደት አያዳግትም:: [8]

በሰሜን ኢትዮጵያ ላይ ባሉ በተለያዩ ቦታዎች ላይ በተደረገ የከርሰምድር ቁፋሮ ጥናት ሳባውያኑ በዚህ ልማድ እንደኖሩ የሚያረጋግጥበት ክፍል አለው:: በየሐ ቀበሌም የጨረቃ ቤተ መቅደስም ዛሬ ድረስ እንደ ቆመ ይህንኑ ታሪክ

ይዘክራል:: ነገስታቱም እስከ አፄ አብርሃ ድረስ «አለመለቀሃ» እያሉ ጨረቃውን ማምለካቸውን የሚገልፁ የድንጋይ ላይ ፅሁፎች (Inscriptions) በብዛት ይገኛሉ:: [9]

ይህ ታሪካዊ መረጃ ተቻኩለው የዩት እንደሆነና በጥቅሉ ከወሰዱት ወደ የተሳሳተ ድምዳሜ (Hasty generalization) እንድንደርስ ያደርገናል:: ስለሆነም ኢትዮጵያዊው ጥንታዊ ዘመን አቆጣጠር የሚጀምረው በጨረቃ ኡደት ነው ወደ ሚለው ሀሳብ ሊያመራ ይችላል:: ነገሩን በጥሞና ስናስተውለው ግን በጥንታዊው የኢትዮጵያ ሥልጠኔ ውስጥ ሶስት ዋና ዋና ታላላቅ የሃይማኖት፣ ማህበረሰባዊ፣ የፖለቲካ ቡድኖች እንደነበሩ የምንገነዘብበት መድረክ ይፈጥርልናል:: እነዚህም ሳባውያን ፣ ኦሪታዊያን እንዲሁም ባህላዊ ሀይማኖት (traditional warship) ተከታዮች የሆኑ አማውያን ወይም /ነባር ህዝብ/ መሆናቸውን እንረዳለን:: [10]



## የምእራፍ ሶስት
## መገናዘቢያ ጥቅሶች

1. ____ .**World History** (vol. I) USA Armed forces institute ( Wisconsin , N.D) p.48 ; See In debth this source; James Brestade (PHD) **Ancient times:A history of the Early world** ( Boston,1916) pp.45,467

2. ይህ መፅሀፍ አዳም ሰባተኛ ትውልድ በሚሆነው በሄኖክ የተፃፈ ነው:: በመፅሀፍ ቅዱስ ገፀ ንባብ በኦሪት ዘፍጥረት ላይ5:1-32 በተጠቀሰው በሄኖክ ይህ መፅሐፍ ተፅፎአል ከሙሴ መነሳት በፊት ሲዘከር የሚከብድ የአለም ሁናቴን የሳለፈው ይህ መጽሐፍ (የጥፋት ውሃ) እና የዘመኑ እርቀት ተያይዞ ስለ ዘመን አቆጣጠር መነሻ ጥንታዊና ብቸኛ እንዲሁም ልዩ መረጃ ያደርገዋል:: ስለ መፅሐፉ ከሙሴና ከኖህ የቀደመ ሆኖ መገኘት ጥያቄ ቢነሳ አበው «ለሙሴ ስለ አዳም የገለጠ መንፈስ ቅዱስ የሄኖክንም መፀሐፍ ለሙሴ ገልጦለት ጽፎታል » ሲሉ ያስረዳሉ:: የኖህ ልጅ የነበረው ቃይናም ከጥፋት ውሃ ከወጡ በኋላ የቀደሙት ሰዎች የፃፉትን ጽህፈት አገኛት አነባበትም ሸሸጋትም እያለ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል የጽሁፍ ስራ ሊተርፍ የሚችልበትን ሌላ ማመልከቻ ይሰጠናል:: (ኩፋሌ 8:35-36) ይህ መፅሀፍ (ሄኖክ) ስለ

ዘመን አቆጣጠር የሚገልፅ ቢሆንም ቅሉ አንድምታዉን ተንትነው የሚያስረዱ የጠሩ ሊቃውንት አበው ካልሆኑ በስተቀር ማንም ተራ ሰው አይቻለውም በመሆኑም አበው በተሰጣቸው ፀጋ አንድ ብለው ስለ መጽሀፉ በጥልቅ እንዲያስረዱ ከማለት ውጭ ፀሀፊው ባለው ውሱንና ኢምንት እውቀት አንዳች ማለት እንደማይቻል ማሳሰብ ይፈልጋል::

3.ማሕበረ ቅዱሳን <u>ዝክረ ዘመን መጪው ዘመን እንደይቀድመን እንነሳ</u> /ሜጋ አሳታሚ 2000 ዓ.ም/ ገፀ 20-27 ዲያቆን በእምነት ምትኩ <u>የኢትዮጵያ ታላቁ ሀብት ባህረ ሀሳበ የዘመን አቆጣጠር</u> /ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ 1999/ ገፅ 1-22 90-115

4. ክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ መነሻው የጌታችን የመድሐኒታችን ልደት ሲሆን ከዚህ ሌላ የጌታን እድሜ በወንጌል ውስጥ እንደ ተጠቀሰው አድርጐ ማነፃፀር የሚችል መሆን አለበት:: የዚህ ዘመን መቁጠሪያን ምዕራባውያኑ የማይጠቀሙት መሆኑ ተረጋግጦአል:: በሚቀጥለው ምእራፍ በስፋት የሚታተት ክፍል ስለሆነ ምእራፍ አምስትን ተመልከት

5. Sergew Habile Sellassie, pp.99, 101,102 See that Constantius wrote to Ezana and Saizana Pleading that frumentius learn ecleastical matters once again from the Arian pope George

6. አስራት ገብረ ማርያም እና ገብረ ሕይወት መሐሪ <u>የዘመን አቆጣጠር</u> /አዲስ አበባ ፤1984/ ገፅ 20-40

7. የጥንታዊ ኢትዮጵያ ታሪክ ብቸኛ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ሰርገው በጥንታዊ ኢትዮጵያ ታሪክ መፅሀፋቸው ገፅ 200 እና 201 ላይ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የግብጽ (ቅብጥ) ቤተ ክርስቲያን ስለ መሆኑ በአፅንኦት ይደመድማሉ:: በይበልጥ ግን ጥንታዊው የግብፅ የጳጉሜ ወር ስግር (sager) እንደሚባል አሳይተዋል:: በኛ በህረ ሀሳብ ላይ ይህን ቃልን የሚጠቀም በመሆኑ በይበልጥ ዋና መረጃችን ያደርገዋል:: ይልቁንም የበጥሊሞስ (ቶለሜ) የፅርእ ንጉሶች ግብፅ ላይ በስልጣን ኑረው የራሳቸውን ቋንቋ እየጨመሩ የመበረዛቸው ስራ በጳጉሜና በተለያዩ በግብፅ ቃላቶች ላይ ትራፊው ዛሬ ድረስ እንዲታይ ምክንያት ሆነዋል ስለሆነም የዚህን ቃል መረጃነት ልብ ማለት አስፈላጊ ነው::

7. Philip K.Hitti, <u>**History of the Arabs: From the earliest times to the present**</u> ( London, 1970) P.87

8. Sergew Habile Sellassie pp.60,117,118

9.ተክለ ፃድቅ መኩሪያ ገፀ 91፤206 ላይ ያለውን በጥንቃቄ በማንበብ ስለ ሀሳቡ ምንነት መረዳት ያስችላል በዚሁ መፀሀፋ / የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጉዬ/ ላይ

ባለው ሶስት ተነፃፃሪ የነገስታት ስም ዝርዝር ላይ ከጌታ ልደት በፊት በኢትዮጵያ የነገሱ ነገስታት ቶማጽዬን ፡ ጽዬን ግዛ እየተባሉ የሚጠሩ እንደነበሩና እነዚህም እንደ እስራኤላውያን ነገስታት እንዳንዶቹ በኦሪት ሲፀኑ በሌላ ጊዜ በዚያው ባለው አምልኮ ሌሎቹ ሲወድቁ የኖሩ ነገስታት እንደሆኑ እንረዳለን:: በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ ኦሪት የገነነችበት በኋላም የምትዳፈንበት እንደገና የምትነሳበትን ሂደት ከነገስታቱ እስከ ህዝቡ ድረስ ያለውን ትስስር ይጠቁመናል::



# ምእራፍ አራት

## ኢትዮጵያ እና ጌታችን በዘመነ ሥጋዌ

ከምድረ እስራኤል እና ከግብጽ ውጭ በአዋልዳት ውስጥ የጌታችን ስደትን አስመልክቶ በስፋት ተጠቃሽ የሆነች ሀገር ኢትዮጵያ ናት ይህንንም በሙላት እና በስፋት የሚያትተው ድርሳነ ኡራኤል ነው::

እንደ አንድምታው አገላለጽ «ወይወርድ እግዚእነ ውስተ ምድረ ግብጽ ተፅዒኖ ዲበ ደመና ቀሊል ወፋኖቶህ ዘእም ዓለም ርኢኩ አእዓዳተ ኢትዮጵያ ይደንግፃ» (የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ) ያለውን መሠረት አይርጐ «ወጐዩ እግዚነ ኢየሱስ ውስተ አድባር ሊባኖስ ወውስተ ምድረ ግብፀ ውብሔረ እግዚእ ምስለ ማርያም እሙ » ይላል ጌታ ከእናቱ ጋር ወደ ደጋማ ተራራ ወደ ግብጽና ወደ ኢትዮጵያ መልእኩ ለዮሴፍ እንደነገረው ስያመነታ ተስደደ ይህም ኢሳያስ ወደ ግብፅ መውረዱን ሲያመለክት ዕንባቆም ደግሞ በዚያው አያይዞ ወደ አትዮጵያ መግባቱን ገልፃል (ትን. ኢሳ 19:1) (እንባቆም 3:6-7) ይላል::

የዋልድባ ገደም ታሪክም ስለ ጌታ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ገዳሙንም የመባረኩን ታሪክ ይገልፅልናል በ1983 ዓ.ም የተተመው የገዳሙን ታሪክ የያዘው መጽሀፍ ስለዚሁ ሲገልጽ እንዲህ ይላል «....[እመቤታችን ከጌታችን ጋር በደመና ሆነው ኢትዮጵያን ሲጐበኙዋት]... ደብረ ዳሞን ተመለከትን

ከዚህ በኋላ አክሱም ደረስን ከአክሱም ተነስተን ደብረ አባይ ደረስን:: ዳግመኛም ከዚህች ቦታ ተነስተን በደመናው ላይ እንደሆን ተከዜን ወንዝ ተሻግረን ዋሊ ከሚባለው ገደም ወይም በርሃ ደረስንና ከዚያ በሚገኘው በርሃ ዋሻ ውስጥ ገባን በዚያችም በረሀ ታላቅ ዋሻ በማግኘታችን እህል እንበላና ውሃም እንጠጣ ዘንድ በውስጧ አረፍን ነገር ግን ምንም የሚበላ አላገኘ ንም ዋሻው የአለው በበርሃ ውስጥ ነበርና ያን ጊዜ ልጄ የብረት አንካሴ ያላት የዬሴፍን በትር ወስዶ የአንዱን እንጨት ሥር ቆፈረ ከእንጨቱም ውስጥ የወጡት ሥሮች 318 ነበሩ:: የአንዱን ሥር አምጥቶ እናቴ ይህን የእንጨት ሥር አንች ብይው አለኝ ያን ጊዜ ልጆ ሆይ ከሰንዱ በቀር ሌላ እንጨት መብላትን አለመድሁም እና ይመረኛል ብዬ መለስሁለት ይህ ይመረኛል የምትይው የእንጨት ሥር ከማር እና ከስኳር ይበልጥ እየጣፈጣቸው የሚመገቡት ቅዱሳን መነኮሳት አሉ (ቋርፋ ነው) አለኝ...ዳግመኛም ልጄ ከኛ ጋር ከግብፀ አገር የመጡትን እነዚህን ሦስቱን አንበሶች በዚህች ገዳም ካሉት አንበሶች ጋር ተደባለቁ አላቸው ምድርን በላይዋ ላይ ሣር በቅሎ እንዳለበሳት እናንተም ብዙ ተባዙና ምድርን ሙሏት አላቸው ልጆቻችሁ እናቴን ለሚወዱ ለቅዱሳን ሁሉ ለሥጋቸው ድካም ማረፊያ እስከ ዓለም መጨረሻ እንደ ፈረስና በቅሎ ለመጓጓዣ ያገልግሏቸው በዚህች ገዳም ውስጥ ያለጥፋት የተባረኩ ሆነው ይኑሩ ብሎ ባረካቸው» ይላል::



በዚህም ታሪክ ላይ የአባ ሳሙኤል አናብስት ለእርሳቸው እንደ በቅሎ ያገለግሏቸው እንደነበረ ከድርሳናቸው ላይ እንረዳለን::

በድርሳነ ኡራኤል ላይ በተጨማሪ ስለ ጌታችን በስደቱ ዘመን ከእመቤታችን ጋር በኢትዮጵያ ምድር እና በግብጽ የተሰደደበትን እና የባረካቸውን ቦታዎች ሁሉ ይዘረዝራል በደቡብ ጎንደርም እመቤታችን በስደትዋ ወቅት ካረፈችባቸው ቦታዎች አንዷ የሆነችው እና ከግብጽ መምጣትዋን የምታጠይቅ ግብጣይት ወይም ግብፃዊት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ትገኛለች::

ድርሳነ ኡራኤል ዘህደር ቁጥር 22 ላይ እመቤታችን ከዮሴፍ አረጋዊ እና ከሰሎሜ ጋር በብርሀት ደመና ላይ ሆና ኢትዮጵያን እንደጐበኘች የአስራት ሀገርዋ ሆና እንድትወስደው አምላካችን ልጅዋ እንደሰጣት ይናገራል::

በቀጥርም 38 ላይ እመቤታችን ከጌታችን ጋር ወደ አክሱም እንደደረሱ በዚያም የኢትዮጵያ ንጉስ ባዜን ታቦተ ፅዮንን ለመሳለም ምምጣቱን በሚያስደንቅ ቋንቋ ያስረዳናል::

በድርሳነ ዑራኤል ላይ እንደተገፈውም እመቤታችን ከኖረችባቸው ቦታዎች ውስጥ ዋና የሆኑት የጣና ደሴቶች ናቸው:: በድርሳኑ ታህሳስ 22 የሚነበበው ክፍል ላይ ስለ እመቤታችን በደሴቲቱ ከጌታጋር ስለ መኖርዋ ይገልፃል:: በቁጥር 22 ላይ እመቤታችን በደሴቲቱ ውስጥ ሥስት ወር

ከ10 ቀን ያህል ተቀምጣለች የሄሮድስንም መሞት እመቤታችን በጥር 18 መላእኩ ኡራኤል እንደነገራት ተጽፎአል::

ዛሬ በየረር ተራሮች ላይ እና በዚያ ባለችው በባእታ ቤተ ክርስታያን እንደሚነገረው እመቤታችን በሰደቷ ወራት አምላክ ልጇዋን ይዛ በብሩህ ደመና ላይ እንዳለች ኢትዮጵያን ስትባርክ በተቀደሰው እግሮቸዋ በየረር ተራራዎች ላይ ባሉት አለቶች ላይ እንዲቆመችባቸው አባቶች ያስረዳሉ::

በዚህም የጌታችን ልደት ዘመንን ለመረዳት እንዲሁም ለማወቅ ግብፁና ኢትዮጵያ ለወንጌሉ ምን ያህል የቀረቡ እንደሆኑ እንረዳለን:: በላይ ባየነው ክፍልም በየቦታው የአምላክ መገለፅን ህዝቡ በትውፊቱ እያስታወሰ እንደሚያወርሰው እና በትውልድ ውስጥ እየቀጠለ መገኘቱንም እናይበታለን::

በተጨማሪም ስለ መፀሀፉ አመጣጥና አፃፃፍ የሚተርክ ክፍል ያለው ሲሆን ፀሐፊው ቅዱስ ዮሀንስ አምጭው ቅዱስ አባ ህርያቆስ እንደሆኑ እንዲህ እያለ ይገልጸዋል:: «ይህ መፀሁፍ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው አምላክን የወለደች የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ቅደሴዋን የደረሰላት በቁስጥንጥንያ ውስጥ በምትገኘው የብህንሳው ኤጲስ ቆጶስ አባ ሕርያቆስ ነው:: ያመጣውም የአክሱም ገበዝ የሚሆን እንበረም ሊቀ ከህናት በነበረበት ጊዜ ሁለቱ የኢትዮጵያ ነገስታት አብርሃና አጽብሐ ከነገሱበት ዘመን በኃላ ነው በጣዕመ ዜማው አንደበቱ የማረ ካህኑ የሬድና አለምን የናቀ የሮሙ ንጉሥ



ጻድቁ አባ አረጋዊ ከንጉሱም ከገብረ መስቀል ጋር ሳሉ ይህንን መጽሐፍ በክብር ተቀበሉ» በማለት በጥቅምት የሚነበበው የድርሳኑ ቁጥር 54-59 ላይ ተፀፎአል:: (ድርሰነ ዑራኤል በግእዝና በአማርኛ አዲስ አበባ ግንቦት 1991 ትንሳኤ ዘጉባኤ)

## ምእራፍ አምስት

## የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ ዩልዮሳዊ ነውን?

በአሁኑ ስአት ሥጋዊው አለም በድምዳሜ የያዘውነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ዮልዮሳዊ ነው! የሚል ከንቱ ሀሳቡ ነው:: ከሁሉ አስቀድሞ ግን ዩልዮስ ቄሳር ስለመሠረተው ዘመን መቁጠሪያ፣ ስለ የግብፅ ዘመን አቆጣጠር ልማድና የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ ስለ አላቸው ባህሪያት በደንቡ መረዳትና ማወቅ ማናቸውንም መላምት ከመዘላበድና የራስን ድብቅ የባህል ወራራ በግልጽ ባዶ በሆነ ተረት ውስጥ አሾልኮ ለማስገባት ሲሞክሩ ከመታየት ያድን ነበር:: ስለነዚህ ዘመን መቁጠሪያዎች ታሪካዊ አመጠጥና ሂደት ጠንቅቆ ማወቁ ያላቸውንም ትስስር ብሎም ልዩነት እንዲሁም የሚያገናኛቸውን መስመር ለመመርመርና ለመረዳት ያስቻላል::


ስለዚህም ይህ አይነቱ ሂደት በጣሙን የላቀና ተቀዳሚ ተግባር ነው:: አንዳንዶች የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ ዮልዮሳዊ ነው ብለው መፃፍቸውን ተከትሎ ሌሎችም (BBC, brodcasting live on Ethiopian millennium clebrations) በቀጥታ ሥርጭት ሳይቀር ይህንኑ መናገራቸውን አጢኖ ይህንን አባባልና ትምህርት ምንነት በቅጡ በማየት ውሳኝ ምላሾችን እንድንሰጥ ያስገድደናል::



ዩልዮስ ቄሳር በ58 ቅ.ል.ክ በሮሜ ከጀነራልነት ተነስቶ አምባገነን ለመሆን የበቃና የቄሳርነትን ማእረግ በሰሙ ያቋቋመ የሮሜ ወታደር ነው:: ይህ ሰው በብዙ ድሎቹና በብዙ ዘመቻዎቹ የተፈራና የታወቀ በኃላም ለስልጣን መንደርደሪያው የጠቀመው ሰው ነበር:: ዩልዮስ በዛ ጓደኞቹ በጩቤ ተወግቶ በ14 «ማርች» ከመሞቱ በፊት አንድ ወሳኝ ስራ ስርቶአል:: ይኸውም በሮማውያን ዘንድ የነበረውን ኋላቀር ዘመን አቆጣጠር ወደ ዘመናዊና ተቀባይነት ያለው ወይም ሊያገኝ ወደሚችል ደረጃ ማምጣት ነበር:: ከዩልዮስ ቄሳር በፊት እንደሚታወቀው የሮማውያን አቆጣጠር በጨረቃ ኡደት ላይ የተመሰረተ የጨረቃ ወሮች ያሉት እና መነሾው ከአፈ ታሪካዊው የሮሜ ከተማ ግንባታ ጋር የተያያዘ ነበር:: እንደ ሮማውያኑ ባህላዊ የዘመን አቆጣጠር ልማድ በሮሙለስ (Romulos) ንግስናና የሮሜ ግንቦታ ለዘመን መቁጠሪያቸው መነሻ እንደሆነ ይናገሩ ነበር::

ሮሙለስ ሬሙስ (Remus) ከሚባለው መንትያው ጋር የነገሳታት ልጆች ነበሩ ይባላል እኒህ ልጆች በተወለዱ ጊዜ በሥልጣን የነበረው አጐታቸው ሲያድጉ መንግስቱን የሚቀሙ ይሆናሉ የሚለውን ንግርት ሰምቶ በጭካኔ ይገደሉ ዘንድ አዝዞ ነበር:: ግደል የተባለው አሽከር ግን ልቡ ስለራራላቸው በቅርጫት ውስጥ ከከተተ በኋላ በታይበር (Tiber) ወንዝ ላይ ለቀቃቸው:: ይህ ወንዝ ዛሬ ሮሜን ለሁለት የሚሰነጥቃት

በመሆኑ ታዋቂ ሆኖ እስከ ዛሬ አለ:: እንቦቃቅሎቹም ከወንዙ ደለል ላይ አርፌው ሲላቀሱ ልጆቸዋ የሞቱባት ተኩላ በመምጣት በመንጋጋዋ እያተሸከመች ወደ ዋሻዋ ወሰዳ አሳደገቻቸው:: እረኛም የሆነ ልጅ የሌለው ሰው በታይበር ወንዝ ደርቻ ሲንቀሳቀስ ልዩ የሆነ ድምጽ ከዋሻዋ ሲወጣ ሰምቶ ቢመጣ ሁለት ደስ ደስ የሚሉ የፋፋና መልከ መልከም ወንድ ልጆች በማየቱ ተደንቆና ተደስቶ ወደ ሚስቱ ወስዶ አኖራቸው:: ባደጉም ጊዜ በጦር ሃይለኛ ሆነው የእረኛውን ዘመዶች እና ህዝቦች (Latins or Ethruscans) የሚባሉት ሳይሆኑ አልቀሩም ተከታይ በማድረግ ጠላቶቻቸውንና አጐታቸውን አጥፋተው የሮሜን ከተማ ተኩላዋ ባዳነቻቸው ስፍራ ላይ መገንባት ጀመሩ::



ስዕል 4 የሮሜ መስራቾች ሮሙለስ እና ሬሙስ



ነገር ግን ታናሽየው ሮሙስ ስልጣን ለታላቁ ይለቅ ዘንድ ምልክቶችና ስምምነቶች ስላስገደዱት ተበሳጭቶ ታላቁን በማንጓጠጥና በመቀለድ «ከተማውን ጠላቶች እንዲህ እያደረጉ ቢያፈርሱትስ ብሎ ቢንደው ታላቁም ተቆጥቶ «እኛም እንዲህ እንመልስላቸዋለን» ሲል በጦር ወግቶ ገደለው:: ይህን አፈ ታሪክን የጥንቶቹ ሮሜዎች ተርከው «የሮሜ አሳዛኝ ግንባታ ለዘመናችን የመጀመሪያ ዓመት ነው::» በማለት ይቆጥሩት እና ይከተሉት ነበረ::[1]

ይህ የዘመን አቆጣጠር በመጋቢት (March) የሚጀመር ሲሆን 10 ወሮችና ከነዚህም መካከል ስድስቱ 30 ቀን ሲኖራቸው አራቱ ብቻ 31 ቀን ያላቸው ነበሩ በጠቅላላው 304 ቀናቶች ያሉት የጨረቃ ኡደትን የተከተለ ነበር ይኸው ዘመን መቁጠሪያ ከሮሙለስ ቀጥሎ መንገሱ በሚነገርለት በኑማ ፖምፓሊየስ (715? - 673?) ቅ.ል.ክ ሁለት ወሮች ተጨምረው ነበር:: እነዚህም ጥርና የካቲት ናቸው ሮማውያኑ ጐዶሎ ቁጥር ባላቸው ወራት ክፉነት ስለሚያምኑ ይህ ንጉስ በጥር ላይ አንድ ቀን በመጨመር 30 ሲያደርገው የካቲትን ደግሞ በ28 ቀናት በመተው በጠቅላላው ከቀድሞው ላይ 51 ቀናት ጨምሮበታል:: ስለዚህ የአመቱ ቀኖች ወደ 355 ደርሰው ነበር ወራቱም ከ10 ወደ 12 አድገዋል ::

በዚህ የአቆጣጠር ልማድ ዘመናትን ያሳለፊት ሮሜዎቹ በ43 ቅ.ል.ክ[2] ላይ ዩልዮስ ቄሳር ከእስክንድርያ

ሶሴጅነስ የሚባል ብልህ የኮከብ ቆጣሪና የዘመን አቆጣጠር አዋቂ አስመጥቶ ይህንን ግራ የተጋባ የዘመን አቆጣጠር ወደ ግብፃውያን ልማድ መልክ ለውጠህ አስተካክልልኝ ስለ አለው እርሱም የጨረቃውን ወር ወደ ፀሀይ የአመቱን ቀን ወደ 365 1/4 ለውጦ የወሮቹን ስሞች በራሳቸው ባህል ባለው ስም እንዲመቻቸው አስተካክሎ ወሮቹንም ወደ 12 ደልድሎ /በሮሚ ልማድ በነበረው አይነት/ አዲስ የዘመን መቁጠሪያ ሰራለት:: ዩልዮስም «የግራ መጋባት ዘመን» በማለት ቁድሞ የነበረውን ዘመን አቆጣጠር ጠራው:: ከአሁን በኋላም የሮሚ መቁጠሪያ ይህ ይሁን ሲል አዋጅን አወጀ::[3]

የጁልየስ ዘመን መቁጠሪያ አቆጣጠር በሁለተኛ አመቱ ይህም በ44 ቅ.ል.ክ ላይ የሮማው ምክር ቤት ይህንን ዘመን መቁጠሪያ እንዲሰራላቸው ላደረገው ለጁልየስ ቄሳር ክብር ሲሉ ኩንታይልስ በመባል ይጠራ የነበረውን ወር ወደ ጁላይ /ጂሊየስ ከሚለው የመጣ/ ቀይረውለታል:: በይበልጥ ዘመን መቁጠሪያውን ላጠናከረውና ታላቅ ሥራን ሰርቷል ብለው ለሚያወድሱት ለአውጉሰጦስ ቄሳርም ክብር ሲሉ ኦገስት የሚባለውን ወር በ8 አመተ እግዚእ (A.D) ላይ ሰይመውለታል:: ከዚያም በኋላ ሮሜ በቅኝ በምትገዛቸው ሀገሮች ላይ ሁሉ ይህ አዋጅ እንዲሰራበት የሚያስገድድ ስለነበረ በአብዛኛው የሮሜ ቅኝ በሆኑ ሀገሮች ላይ ይህ አዋጅ ሊፀና ችሎአል::



ይህ በዚህ ሁናቴ እየቀጠለ በመሄድ ዘመን በዘመን ላይ ተፈራርቆ አምስት መቶ አመታትን ካሳለፈ በኋላ አንድ አዲስ ሀሳብ መነጨ:: አስቀድሞ የሮሜ መንግስት ክርስትናን ለማጥፋት ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም:: በጌታችን ዘመነ ሥጋዌውም ቢሆን አይሁድ ከሳሽ ሲሆኑ ሰቃይ ደግሞ የሮሜ መንግስት ነበር:: እየዋለ ሲያድር ግን እነ ኔሮ የመሳሰሉትን ብሎም እነ ማርከስ አውሬሊየስ የሚባሉትን ፀረ ክርስትና ቄሳሮች ያቀፈ ኤምፓየር ሆኖ ተገኘ

ቆስጠንጢኖስ በ313 እ.ኤ.አ የክርስትና ህጋዊነትን እስኪያውጅ ድረስ በሮማ አለም ውስጥ ክርስቲያኖች የመኖር ያህል እንኳን ቦታ አልነበራቸውም::ድል የአምላክ ነውና ክርስትና መከራውን አልፋ ማሸነፍዋን የተገነዘቡት የሮሜ ገዢዎች በጣኦት አምላኮ ላይ የተገነባው ባህላቸው አብሮ ሊያከትም መሆኑን ለመረዳት ጊዜ አልወሰደባቸውም:: ስለዚህ አዲስ የሆነ ዘመን አቆጣጠርና የድሮውን ማንነታቸውን የሚሸፍን ሌላ ታሪክ ማስመዝገብ ፈለጉ::

በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዲዮናሲዮስ ኤክሲጀስ (Dionysius Exigus) የተባለ መነኩሴ ስለ ጌታችን የልደት ዘመን የግሉን ጥናት ካካሄደ በኋላ ቅደመ ልደተ ክርስቶስ እንዲሁም ከጌታችን ልደት በኃላ ያለው አመት ወይም አመተ እግዚእ ( Before christ and Anno Domini) በማለት ከፋፍሎ ጌታ ተወልዶበታል ያለውን ግምታዊ አመት

በማሳወቅ የሮሜ ነገስታት በሙሉ በዚህ እንዲመሩ በጽጽስናው ስልጣን ተጫናቸው። ይህንን በመያዝ የዩልዮስን ዘመን አቆጣጠርን አሻሽለው ሌሎች አስር መቶ አመታትን ካሳለፈ በኋላ ዮልዮስ የቀመረው ዘመን መቁጠሪያ በ11 ደቂቃ ከ14 ስኮንድ ከእውነተኛው የፀሀይ ኡደት በሽራፊው 1/4 ቀን ምክንያት የቀደመ ነው በማለት በ1582 አመተ እግዚእ ላይ በፓፓ ግርጎሪዮስ አስራ ሰምንተኛው ወሳኔ ተሻሽሎ ዛሬ ድረስ የሚከተሉት ሆኖነዋል። [4]

ዛሬ ላይ ደግሞ በግል ጥናትና መላ ምት የሃይማኖትን ነገር አስረዳለሁ የሚለው የምዕራቡ አለም ቀድሞ እንደ ጨረባ እነ ኤክሲጀስ የነገሩዋቸውን ሲደግሙ ኖረው ዛሬ ደግሞ በጥናት እንዳረጋገጡት «የኤክሲጀስ ግምት በአራት አመት የቀደመ ነው» ሲሉ በአራት አመት የአሁኑ ዘመን መቁጠሪያቸው እንደሚዘገይ እንዲሁም የተበላሸ ወይም እውነተኛ እንዳይደለ ይመሰክራሉ [5]

በዚህች እንኳን ማስረጃ ብንነሳ ዛሬ 2007 A.D የተሰኘው አመት በነርሱ ጥናት መሰረት ስህተት ሆኖ ትክክለኛው 2003 አ.እ የሚለው ከሆነ ለዚህ እንኳን ዘመን በመጠጋት ወደ ትክክለኛነት የሚያመዝነው የኢትዮጵያዊው 2000 ዓ.ም ዘመን መቁጠሪያ ነው። ምንም እንኳን በሚቀጥለው ክፍሎች ስለ ኢትዮጵያዊው ዘመን መቀጠሪያ ትክክለኛነት የምንገልፅ



ቢሆንም በቀላሉ እንኳን ነጭጮቹ እርስ በእራሳቸው የሚነጋገሩት እና የሚያስተምሩት ምን ያህል የሚጣረስና የሚጋጭ መሆኑን ለማሳየት ብቻ ሲባል ይህንን ለማምጣት ተገድደናል።

ይህ እንግዲህ ስለ ዮልዩናዊው ዘመን መቁጠሪያ በአጭሩ የሚገልጽ ከሆነ አንድ ሰው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ዩልዮሳዊ ነው ለማለት የሚያስችለው ምን ተጨባጭ መረጃ ይኖረዋል።

የዩልዮስ ዘመን መቁጠርያ በ30 እና በ31 ቀን የተከፋፈለ እንዲሁም የካቲት ላይ 28 ቀን ያሉት ዘመን መቁጠሪያ ነው። የኛስ? የዮልዮስ ዘመን አቆጣጠር በራሳቸው ስያሜ የተሰየሙ ወሮች እሉት እነ ኦገስት እና ጁላይ ደግሞ ከየት እንደመጣ በየትም ባህል ውስጥ ባእድ የቃል ዘር በመሆን ምንጩን ይገልፁ ነበር። የዩልዮስ ዘመን መቁጠሪያ 12 የውር ድልደል ሲኖረው እኛ 13 አለን ታዲያ እንዲሁ በፍፁም የአይምሮ ጨቅላነት በሚሰተዋልበት እነዚህን መሠረታዊ ልዩነቶችን ሳያዩ ዩልዮሳዊ ዘመን መቁጠሪያን ኢትዮጵያ ትጠቀማለች ለማለት የሚገፋፋ አለማ ምን ይሆን? ዮልዮስ አዋጁን ባወጀበት ሰአት በሮሜ ቅኝ ያሉ ሀገሮች ሁሉ እንዲከተሉት ያስገደደ ነበር። በመሆኑም የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጣር ዩልዮናዊ ነው ማለት ከተፈለገ ኢትዮጵያ የሮሜ ቅኝ ተገዢ ነበረች ማለት ነው ወደሚለው መምጣት

ያስፈልጋል ታሪክ ግን ኢትዮጵያ የሮሜ ቅኝ ተገዢ ነበረች አይልም ይህ አባባል ስለዚህ በየዋህነት የተሰነዘረ ከሆነ ፍፁም ስህተቱን በተንኮል የተወረወረ ከሆነ ደግሞ ክፉ ምኞቱን የሚያስይ ከመሆን ውጭ ምንም ረብ የሌለው ነው።

ሮሜዎች እንኳን ታላቅ ስልጣኔ አለን እያሉ ሲኖሩ ስለ ዘመን አቆጣጠር የግብፅ ሊቅ አስተማሪ አስፈልጓአቸዋል። ከዚህም በመነሳት እንኳን ለኢትዮጵያ ጥንታዊ ስልጣኔ ቀርቶ ለሌሎችም ቢሆን ስለ ዘመን አቆጣጠር ምንም የሚያስተምሩትና የሚዘክሩት የሌላቸው ተማሪዎች መሆናቸውን እንረዳለን ስለሆነም ደግሞ የኛ ዘመን አቆጣጠር ዩልዮናዊ ሊሆን እንደማይችል ያረጋግጥልናል። በተጨባጭ ታሪካዊ መረጃዎች ላይ እንደተቀመጠው እና ከላይ እንዳየነው የኢትዮጵያን ዘመን አቆጣጠር በማስተዋል ረጋ ብሎ ላጠና ሰው ምንጩ ቅብጥ በሀዲስ ኪዳን ስለመሆኑ አያጠራጥርም ያም ባለፈው ምእራፍ በሰፊው ታትቷል።



## ምእራፍ አምስት ማገናዘቢያ ጥቅሶች


1. see Horniblow and Sullivan , **The March of Time mighty men and mighty deeds** (london, 1949)P.19; አስራት ገብረ ማርያም እና ገብረ ህይወት መሀሪ ገፅ 20-21

2. ሁል ጊዜ ቅ.ል.ክ. ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ማለት ሲሆን የአውሮፖውያኑን አቆጣጠር የሚያመለክት መሆኑን መረዳት ይገባል።

3. **The New encyclopedia Britannica** S.V. Calendar Vol. XV. (Chicago, 1993) pp.184-92,187,421-432,

4. Ibid, P.430

5 **Comptions encyclopedia** S.V. Calender; (university of chicgo, 1983) pp.28-29; **Seven day Adventist Bible commentary In seven Volumes** Vo1.5. (Review and Herald publishing Assoication, 1956) S.V Herod. P. 42.